# የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETTE
# OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሠላሳኛ አንደኛ ዓመት ቁጥር ፴፱
አዲስ አበባ ሚያዚያ ፴ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

31st Year No. 39
ADDIS ABABA, 7 th, May, 2025


**<u>ማውጫ</u>**

**አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፶፮/፪ሺ፲፮ ዓ.ም**


የኢትዮጵያ የሕንፃ አዋጅ………………ገፅ ፲፰ሺ፪፻፷፪


**<u>CONTENT</u>**

Proclamation No. 1356/2024


Ethiopian Building Proclamation ……Page 18262


## <u>አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፶፮/፪ሺ፲፮</u>
## <u>የኢትዮጵያ የህንጻ አዋጅ</u>

የሕንፃ ግንባታ ወይም የሕንፃ ግንባታ ማሻሻያና የአገልግሎት ለውጥ ስራ የሕዝብ ጤንነትና ደህንነት መጠበቅ እና የህንጻ ተደራሽነት እና ተጠቃሚነትን ለአካል ጉዳተኞች እንዲሁም ልዩ ድጋፍ ለሚሹ እና ለጠቅላላ የማህበረሰብ ክፍሎች ማረጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

ፀድቀው በትግበራ ላይ የሚገኙትን የኢትዮጵያ የህንፃ ስታንዳርዶች በሁሉም የህንፃ ግንባታዎች ላይ አስገዳጅ ሆነው አገልግሎት ላይ እንዲውሉ መደንገግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

## <u>PROCLAMATION NO. 1356 /2024</u>
## <u>ETHIOPIAN BUILDING PROCLAMATION</u>

**WHEREAS**, building or building improvement and service transformation work where it is necessary to protect public health and safety and ensure access and accessibility of buildings to persons with disabilities as well as those in need of special support and to the general community as a whole;

**WHEREAS**, it is necessary to enact the enforceability of Building Codes of Ethiopia that are being implemented and enforcing them on all building constructions;


ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001



https://ethiodata.et/

በነባሩ ሕግ በአፈፃፀም የተለዩ የመልካም አስተዳደር ችግሮች፣ የአካል ጉዳተኞችን ተደራሽነት በሚያረጋግጥ፣ የግንባታ ጥራትና የሀብት ብክነት ችግሮች ለመቅረፍ የሚያስችል ግልፅና ለአተገባበር ምቹ የሆነ የአሰራር ስርዓት መዘርጋት ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፩/፫/ መሠረት የፌደራሉ መንግስት የጤና፣ የትምህርት እንዲሁም የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሀገር አቀፍ መመዘኛዎችንና መሠረታዊ የፖሊሲ መለኪያዎችን የማውጣትና የማስፈፀም ሥልጣን የተሰጠው በመሆኑ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭/፩/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### ፩.አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ የሕንፃ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፶፮/፪ሺ፲፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

### ፪.ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩/ "የግንባታ ክትትልና ቁጥጥር" ማለት ግንባታ ፈቃድ የተሰጣቸው የህንጻ ግንባታዎች ተገንብተው እስከሚጠናቀቁ

**WHEREAS,** it is appropriate to establish a transparent and easy-to-implement system to address the problems of good governance, accessibility for disabled person, construction quality and wastage of resources identified by the existing law;

**WHEREAS,** the Federal Democratic Republic of Ethiopia Government is given with the power to issue and execute health, education as well Science and Technology National requirements and basic policy measurements according to the FDRE Constitution Article 51/3/; now, therefore, in accordance with Article 55 (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is Proclaimed as follows.

## PART ONE
## GENERAL PROVISIONS

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as "Ethiopian Building Proclamation No.1356/2024".

### 2. Definition

In this Proclamation unless the context provides otherwise.

1/ "Construction Control and Supervision" means a system that follows up and monitors new, temporary, permanent, and

https://ethiodata.et/

ድረስ የሚደረግ የቁጥጥርና ክትትል ሥርዓት ነው፡፡

፪/ ህንጻ" ማለት ማንኛውም በምድር፣ ከምድር በታች ወይም በላይ ወለል ጣሪያ እና ይዘት ያለው ከአርማታ፣ ከብረት ወይም ከሌሎች ቁሶች የተሰራ ለመኖሪያ እና ለሌሎች አገልግሎቶች የሚውል ቋሚ ግንባታ ነው።

፫/"የህንፃ ባለሙያ" ማለት አርክቴክት፣ ስትራክቸራል ኢንጂነር፣ኤሌክትሪካል ኢንጂነር፣ መካኒካል ኢንጂነር፣ ኤሌክትሮ መካኒካል ኢንጂነር እና ኳንቲቲ ሰርቬየር ባለሙያ ማለት ነው።

፬/ "የህንጻ ሹም" ማለት በከተማ አስተዳደር ደረጃ የሚቋቋም የህንፃ ግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር የሚፈፅም እና የሚያስፈፅም የፅህፈት ቤት ኃላፊ ወይም የሥራ መሪ ወይም አስተባባሪ ሲሆን በሕንጻ እና ተጓዳኝ ዘርፎች በቂ የትምህርት እና የሙያ ዝግጅት ያለው የተመዘገበ ከፍተኛ የህንፃ ዲዛይን ባለሙያ ነው፡፡

፭/ "አሠሪ" ማለት ግንባታ ለማከናወን የግንባታ ፈቃድ ወስዶ የሚገነባ ወይም የሚያስገነባ የህንጻ ባለቤት ነው፡፡

፮/ "የተመዘገበ ባለሙያ" ማለት ሥልጣን ባለው አካል ተመዝግቦ በዲዛይን ወይም በቁጥጥር ስራ ባለሙያነት የምዝገባ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው ነው፡፡

renovated buildings until they are completed.

2/ Building" means any permanent construction made of metal, or other materials, on earth underground,or above the surface,for residential and other uses.

3/ Building Officer" means an Architect, Structural Engineer, Electrical Engineer, Mechanical Engineer, Electro-Mechanical Engineer, and Quantity Surveyors.

4/ Building Officer" means an officer or manager or coordinator who executes and executes building permits and inspections at the city government level and is a registered senior professional with adequate educational and professional preparation in the building and related sectors.

5/ "Employer" means an owner who takes a building permit for building on his own or giving contracts for construction.

6/ "Registered Expert" means an individual who is registered with an authorized body and has been certified as a professional in design or construction.

https://ethiodata.et/

፯/”የተመዘገበ ከፍተኛ የህንፃ ዲዛይን ባለሙያ” ማለት በዲዛይን ወይም በቁጥጥር ስራ ባለሙያነት የምዘገባ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው ነው፡፡

፰/“የተመዘገበ የሥራ ተቋራጭ” ማለት ሥልጣን ባለው አካል ተመዝግቦ የሥራ ተቋራጭነት የምዝገባ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው ነው፡፡

፱/“ምድብ ‘ሀ’ ሕንፃ” ማለት ማንኛውም ከምድር በላይ ሁለት ፎቅና ከዚያ በታች ወይም ምድርና ከምድር በታች አንድ ወለልና ከዚያ በታች የሆነ ሕንፃ ወይም በሁለት ቋሚ ተሸካሚ የአርማታ ወይም የብረት ወይም ሌሎች የስትራክቸራል ውቅሮች መካከል ከ ሰባት /፯/ ሜትር ያልበለጠ ርቀት ያለው ባለአንድ ፎቅ የመኖሪያ ሕንፃ ነው፡፡

፲/ “ምድብ ‘ለ’ ሕንፃ” ማለት ማንኛውም ከምድር በላይ ከሁለት ፎቅ እስከ አራት ወይም ምድርና ከምድር በታች እስከ ሁለት ወለል ያለው የግል ወይም የጋራ መኖሪያ ሕንፃ ወይም በሁለት ቋሚ ተሸካሚ የአርማታ ወይም የብረት ወይም ሌሎች የስትራክቸራል ውቅሮች መካከል ከ፯ ሜትር በላይ ሆኖ ከ፲፪ ሜትር ያልበለጠ ርቀት ያለው ባለ አንድ ፎቅ ሕንፃ ወይም በከፍታና ስፋት በምድብ ‘ሀ’ ደረጃ የሚታዩ የሪል እስቴት ቤቶችን ይጨምራል፡፡

7/ “Registered Senior Building Design Professional” means an individual that has been granted a certificate of registration as a professional or control work;

8/ “Registered Contractor" means a person who has been registered with an authorized body and issued a certificate of registration as a contractor;

9/ "Category 'A' Building" means any one-story building with a height of not more than 7 meters between two floors above or below the ground floor or between two permanent concrete or steel or other structural members.

10/ "Category 'B' Building’’ means private or apartment with five story and lessee and more than two story above the ground level; any single-story building with a height of more than 7 meters above the ground and no more than 12 meters between two or more vertical concrete or steel or other structural members building, or includes Category ‘A’ in height and width such as real estate.

https://ethiodata.et/

፲፩/ "ምድብ 'ሐ' ሕንፃ" ማለት ማንኛውም ከምድር በላይ ከ ፭ ፎቅ እስከ ፲፪ ወይም ምድርና ከምድር በታች ከ፫ እስከ ፬ ወለል ያለው የግል ወይም የጋራ መኖሪያ ሕንፃ ወይም በሁለት ቋሚ ተሸካሚ የአርማታ ወይም የብረት ወይም ሌሎች የስትራክቸራል ውቅሮች መካከል ከ፲፪ ሜትር በላይ ሆኖ ከ ፲፱ ሜትር ያልበለጠ ርቀት ያለው ባለ ሁለት ፎቅ ሕንፃ ነው፡፡

፲፪/ "ምድብ 'መ' ሕንፃ" ማለት ማንኛውም ከምድር በላይ ከ፲፪ ፎቅ በላይ ወይም ምድርና ከምድር በታች ፭ እና ከዚያ በላይ ወለል ያለው ሕንፃ እና በሁለት ቋሚ ተሸካሚ የአርማታ ወይም የብረት ወይም ሌሎች የስትራክቸራል ውቅሮች መካከል ከ፲፱ ሜትር በላይ ርቀት ያለው ባለ ሦስት ፎቅ ሕንፃ እንዲሁም ማንኛውም የሕዝብ መገልገያ ወይም ተቋም ነክ ሕንፃ ወይም የወርክሾፕ፣የፋብሪካና ኢንዱስትሪ ሕንፃ ነው፡፡

፲፫/ "ግንባታ" ማለት አዲስ ሕንፃ መገንባት ወይም ነባር ሕንፃን ማደስና ማሻሻል ወይም አገልግሎቱን መለወጥ ወይም ሕንፃን የማፍረስ ሂደት ነው፡፡

፲፬/ "የግል መኖሪያ ሕንፃ" ማለት ለመኖሪያነት የሚያገለግሉ አንድ ወይም ከአንድ በላይ ክፍሎችና የመፀዳጃና የማብሰያ አገልግሎቶች ያሉት ሆኖ በቅጥር ግቢው ውስጥ የሚገኝ የመኪና ማቆሚያንና

11/ "Category 'C' Building" means any building above five floors above the ground; or a one-story building with a height of more than 12 meters between the ground and five floors and above or between two permanent concrete or steel or other structural structures;it is also a public utility or institution-related building or workshop, factory and industrial building.

12/ "Category 'D' Building" means any building of more than twelve stories above the ground or five or more floors above the ground, or a three-story building with a distance of more than 19 meters between two fixed-bearing concrete or steel or other structural configurations. It is also any public utility or institution-related building or workshop, factory and industrial building.

13/ "Construction" means the process of building a new building or renovating an existing building or changing its services or demolishing a building;

14/ "Private Residential Building" means one or more living quarters withtoilets and cooking services, may include parking in the premises and separate rooms from the main house to be used as residences;

https://ethiodata.et/

ለመኖሪያነት የሚውሉ ከዋናው ቤት የተነጠሉ ክፍሎችን ሊጨምር ይችላል፤

፲፭/"ፎቅ" ማለት በሁለት ወለሎች መካከል ወይም ከላይ ሌላ ወለል ከሌለ በወለሉና በኮርኒስ መሃል ያለው የሕንፃ ክፍል ነው፤

፲፮/"ሪል ስቴት" ማለት በመሬት ላይና ውስጥ ያሉትን የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች ያካተተ ይዞታ ነው፣

፲፯/"ጊዜያዊ ግንባታ" ማለት የጊዜ ገደብ ተቀምጦለት ጊዜያዊ ለሆነ አገልግሎት ታስቦ የሚገነባ እና የተሰጠው የጊዜ ገደብ ሲጠናቀቅ የሚነሳ የሕንፃ ግንባታ ነው፡፡

፲፰/ "የግንባታ ፈቃድ" ማለት አዲስ ህንጻን ለመገንባት ወይም ነባር ህንጻን ለማሻሻል ወይም አገልግሎቱን ለመለወጥ እንዲሁም ለማፍረስ ሲፈለግ ሕንፃውን ለመገንባትና ለማፍረስ የሚያስችሉት ዝርዝር መስፈርቶች እንደተሟሉ ተረጋግጦ ግንባታ እንዲካሄድ ፈቃድ መሰጠቱን የሚገልጽ ማስረጃ ነው፡፡

፲፱/"የሕንፃ መጠቀሚያ ፈቃድ" ማለት በምድብ "መ" ስር የሚካተት አዲስ ህንፃ የግንባታ ስራው ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ሲጠናቀቅ፤ ወይም ነባር ሕንፃ ባለበት ሁኔታ የአገልግሎት ለውጥ ወይም ማስፋፋት ወይም ማሻሻያ ተደርጎበት ሲጠናቀቅ እንዲሁም የህዝብ

15/ "Floor" means the part of a building between two floors or between the ground and the ceiling if there is no other floor above;

16/ "Real Estate" is a property that includes real estate on and off the ground.

17/ "Temporary Construction" means the construction of a building that is scheduled for temporary use having time schedule set for it and will be removed at the end of the given period;

18/ "Construction Permit" means proof that a building permit has been issued for the construction of a new building or for the renovation of an existing building or change the service certifying the details of requirements to construct the building are fulfilled.

19/ "Building use Permit" means license given when a new building under Category "D" is fully or partially completed; or when a existing building is finished with the service change or expansion or renovation as well the public utility building is upgraded in terms of accessibility for people with

https://ethiodata.et/

መገልገያ ህንፃ ከአካል ጉዳተኞችና ልዩ ድጋፍ ለሚሹ የማሕበረሰቡ ክፍሎች ተደራሽነት እና ተጠቃሚነት አኳያ ሲሻሻል ደህንነቱ ተረጋግጦ ጥቅም ላይ ለማዋል የሚሰጥ ፈቃድ ማለት ነው፤

disabilities and people who need special support.

፳/“አስጊ ሕንፃ” ማለት ግንባታው የአገልግሎት ዘመኑ የተጠናቀቀ ወይም አገልግሎት መስጠት የማይችል መሆኑ የተረጋገጠ ህንጻ ነው፡፡

20/ "Dangerous Building" means a building in which its service life has expired or is inoperable.

፳፩/ “ሰነድ” ማለት ከሕንፃ ዲዛይንና ግንባታ ጋር በተያያዘ የሚያስፈልግ ወይም የተዘጋጀ ፕላን፣ ሪፖርት፣ የዋጋ ግምት ወይም ማንኛውም የቴክኒክ ጉዳይን የሚያስረዳ ሰነድ ነው፡፡

21/ "Document" means a plan, report, cost estimate or document briefing any other technical issue related to the design and construction of a building;

፳፪/ “የፕላን ስምምነት” ማለት ለሕንፃ ግንባታ እንዲቀርብ ለሚዘጋጅ ዲዛይን ከከተማው ፕላን ጋር የተጣጣመ እንዲሆን የሚያስችለው መሆኑን በማረጋገጥ የሚሰጥ በአንድ ቦታ ሊገነቡ የሚችሉ እና ለቦታው የተፈቀዱ የአገልግሎት አይነቶችን፣ለቦታው የተፈቀደ የሕንፃ ከፍታን፣ የመዳረሻ መንገድ ጠለል ከፍታን፣በቦታው አካባቢ የሚያልፉ የመሠረተ ልማት አውታሮችን እንዲሁም በቦታው አሁን ያሉ እና የታቀዱ የግንባታ መጠን የሚያሳይ የፕላን መረጃ ነው፤

22/ “Plan Agreement” means that the plan information given certifying the design produced to be lodged for the construction of a building is fit to be in conformance with the city plan displaying the types of services that can be built in one place, the height allowed for the building, the infrastructure that will pass through the site, and the current and planned construction;

https://ethiodata.et/

፳፫/“የኢትዮጵያ የህንጻ ስታንዳርዶች” ማለት ተሻሽለው ወይም በአዲስ መልክ ተዘጋጅተው ስራ ላይ የዋሉ በሀገሪቷ ለሚገነባ ማንኛውም ህንጻ ዲዛይን ሲዘጋጅ የሚያገለግሉ የህንጻ ስታንዳርዶች ናቸው፤

፳፬/“ዲዛይን” ማለት የአንድን ሕንፃ መጠን፣ ዓይነትና ስፋት እንዲሁም ሕንፃው የሚሠራበትን ቁሳቁስና የአገነባብ ዘዴን የሚያሳይ ለሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች ተደራሽነትን የሚያመላክት ንድፍ ወይም ሞዴል ሲሆን የአርክቴክቸር፣ የስትራክቸር፣የሳኒተሪ፣ የኤሌክትሪካል፣ የመካኒካል፣ ኤሌክትሮ-መካኒካል፣ የእሳት መከላከልና የቴሌኮሚዩኒኬሽንና ሲግናል የሌሎች ሥራዎችን ጥናት፣ ትንተና እና ንድፍ ያካተተ ነው፡፡

፳፭/“ሁሉን አቀፍ ንድፍ“ ማለት በተቻለ መጠን ማሻሻያ ወይም ልዩ ንድፍ ሳያስፈልገው አካል ጉዳተኞችን ጨምሮ ለሁሉም ሰው ጥቅም ላይ መዋል እንዲችል ሁሉን አቀፍ ተደርጎ የሚነደፍ ምርት፣አካባቢ፣ፕሮግራምወይም አገልግሎት ነው፡፡

፳፮/ “የአገልግሎት ለውጥ” ማለት አንድ ሕንፃ ሲሰጥ የነበረውን አገልግሎት በሌላ የአገልግሎት ዓይነት መለወጥ ነው፡፡

23/ "Ethiopian Building Standards" means standards that have been revised or redesigned which are into practice that specify the requirements for any building design or construction in the Country.

24/ "Design" means a design or model of a building's size, type and size, as well as the materials and construction methods used in the building,and includes the architecture, stricture, sanitary, electrical,mechanical,electro mechanical, fire fighting,Telecommunication and other works survey, analysis, and design.

25/ ”Universal Design” means a product environmental, program or service that is designed to be all accessible to everyone including people with disable, without the need for modification or special design as much as possible;

26/ "Service Change" means the building change of service from one to another;

https://ethiodata.et/

፳፯/ "የማስቆሚያ ትዕዛዝ" ማለት በአንድ የሕንፃ ግንባታ ቦታ የሚካሄድ እና የህግ ጥሰትን ተከትሎ ሥራ እንዲቋረጥ ወይም እንዲቆም በተቋሙ ወይም በሕንፃ ሹም የሚሰጥ ትዕዛዝ ነው፡፡

27/ "Stoppage Order" means an order issued by a building officer to terminate or stop work on a building site;

፳፰/"ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር" ማለት እንደቅደም ተከተሉ የከተማ እና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፡፡

28/ "Ministry or Minister" means according to the order of priority it is referred as the Ministry or Minister of Urban and Infrastructure;

፳፱/"ክልል" ማለት በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፵፯ መሠረት የተቋቋመ ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ ከተማና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችን ያካትታል፡፡

29/ "Region" means a region established in accordance with Article 47 of the FDRE Constitution and includes the Addis Ababa and Dire Dawa City administrations.

፴/"ከተማ" ማለት ማዘጋጃ ቤት ወይም ሌላ ስያሜ ቢኖረውም ተመሳሳይ አገልግሎት ሰጪ የመንግስት አደረጃጀት የተቋቋመበት ወይም ፪ሺ ወይም ከዚያ በላይ የሕዝብ ቁጥር ያለውና ከዚህ ውስጥ ቢያንስ ፶ በመቶ የሚሆነው የሰው ኃይል ከግብርና ውጭ በሆነ ስራ የተሰማራ ሆኖ የሚገኝበት አካባቢ ነው፡፡

30/ "City" means an area with a municipal or other designated similar service organization or with a population of 2,000 or more and at least 50% of the workforce engaged in non-agricultural activities.

፴፩/ "የከተማ አስተዳደር" ማለት በሕግ ወይም በሚመለከተው መንግሥታዊ አካል ውክልና የከተማ አስተዳደር ሥልጣንና ተግባር የተሰጠው አካል ነው፡፡

31/ "City Administration" means a body given with the duties and responsibilities as the city administrator by law or by the delegation of the relevant government body;

፴፪/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

32/ "Person" means a natural person or juridical entity;

https://ethiodata.et/

፴፫/በዚህ አዋጅ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

፫. **<u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>**

፩/ ይህ አዋጅ በሚከተሉት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል:-

ሀ) በዚህ አዋጅ አስር ሺ እና ከዚያ በላይ ነዋሪዎች ባላቸው ከተሞች፤

ለ) ከከተማ የአስተዳደር ወሰን ውጭ በሚገኙ ህዝብ የሚገለገልባቸው ሕንፃዎች፣ የኢንዱስትሪ ወይም የዘመናዊ እርሻ ተቋሞችና የሪል ስቴት ሕንፃዎች፡፡

፪/ ክልሎች አዋጁ ተፈፃሚ እንዲሆን በሚመለከተው አካል ባስወሰኑባቸው ሌሎች ከተሞች፣

፫/ ይህ አዋጅ በሚከተሉት ላይ ተፈፃሚ አይሆንም:-

ሀ) አዋጁ በፀናበት ቀን ወይም ወይም ከዚያ በፊት በተጠናቀቀ ህንፃ፣

ለ) አዋጁ ከፀናበት ቀን በፊት በተሰጠ የሕንፃ ግንባታ ፈቃድ በመካሄድ ላይ በሚገኝ በማናቸውም ሕንፃ፣

ሐ) ከሀገር ደህንነት ጋር በተያያዘ እና በሌሎች ምክንያቶች አዋጁ ተፈፃሚ እንዳይሆንበት በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወሰን ሕንፃ፡፡

33/ The provisions of this Proclamation for the masculine gender also include the feminine;

3. **<u>Scope of Application</u>**

1/ This Proclamation shall apply to the following:

a) Cities that meet the requirements of urban center under this Proclamation;

b) Public buildings, industrial or modern agricultural facilities and real estate buildings outside the city limits.

2/ In other Cities where the Regions have decided to implement this Proclamation;

3/ This Proclamation shall not apply to the following in:

a) the building completed on or before this Proclamation

b) any building under construction permit issued before the effective date of the Proclamation.

c) a building determined by the Council of Ministers to prevent the Proclamation from being implemented in connection with

https://ethiodata.et/

፬/ የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፫ (ሀ) እና (ለ) ድንጋጌ ቢኖርም ከዚህ በታች በተዘረዘሩት ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡-

ሀ) የህንጻ አዋጁ ከመውጣቱ በፊት ለተገነቡ ነባር ህንጻዎች ባለበት ሁኔታ አካል ጉዳተኞችንና ልዩ ድጋፍ ለሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች ተደራሽና ተጠቃሚ ለማድረግ ማሻሻያ ለሚያስፈልጋቸው የህዝብ መገልገያ ህንጻዎች፤

ለ) ለህዝብ ደህንነትና ጤንነት አስጊ የሆኑ ህንፃዎች ለማስተካከል ወይም እንደአስፈላጊነቱ ለማፍረስ፤

ሐ)ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት በወጣ የሕንፃ ግንባታ ፈቃድ መሠረት በመካሄድ ላይ የሚገኝ ሆኖ ግንባታው ይህ አዋጅ ከፀናበት ቀን ጀምሮ በሦስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ያልተጠናቀቀ ከሆነ፣

መ) የአገልግሎት ለውጥ ወይም የእድሳት ጥያቄ የሚቀርብለት ህንፃ ሕንፃው ሊሰጠው ከታሰበው አገልግሎት አንፃር ደረጃውን የጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ፣

ሠ) የእድሳት ፈቃድ ጥያቄ በሚቀርብለት ህንፃ ላይ ተቋሙ ይህ አዋጅ ተፈጻሚ እንዲሆንበት ያደርጋል፡፡

national security and other reasons.

4/ Notwithstanding the provisions of sub-Article 3 (a) and (b) of this Article,it is applicable on the following:

a) existing public buildings which were built before the Proclamation that needs upgrading due to inaccessibility for people with disabilities of the building Proclamation;

b) to rehabilitate or demolition buildings that are dangerous to public safety and health.

c) if the construction is not completed within three years from the effective date of this Proclamation, which is being carried out in accordance with the building permit issued prior to its promulgation;

d) to ensure that the building in request for change of service is in line with the intended service.

e) when there is a request for renewal permit, the institution may enforce this Proclamation.

https://ethiodata.et/

## ክፍል ሁለት

## ስለአስፈጻሚ አካል

**፬.የሕንፃ ግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር አስፈጻሚ አካል ስለማቋቋም**

፩/ አዋጁ ተፈጻሚ በሚሆንባቸው ከተሞች የህንጻ ግንባታ ፈቃድ እና ቁጥጥር የሚመራ እና የሚያስፈጽም የህንጻ ግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ተቋም ወይም ከዚህ በኋላ “ተቋም ” እየተባለ የሚጠራ ከነባሩ አደረጃጀት ጋር በማጣጣም የስራ መደራረብን ሊያስቀር በሚችል መልኩ የሚቋቋም ይሆናል፡፡

፪/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፩ የተደነገገው ቢኖርም የህንፃ ግንባታ ፈቃድ እና ቁጥጥር ስራዎችን የሚመራ ተቋም ስያሜና አደረጃጀት ክልሎች ከራሳቸው ተጨባጭ ሁኔታ በመነሳት በሕግ ይወስናሉ፡፡

፫/ ተቋሙ አጠቃላይ ስራውን የሚመራ ለመስኩ ተዛማጅ የሆነ የትምህርት ዝግጅትና የስራ ልምድ ያለው የህንፃ ሹም ወይም እንደየ ክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ በሕግ የሚወሰን ስያሜ የሚሰጠው የሥራ ኃላፊ እንዲሁም በስሩ ለሚፈፅማቸው ተግባራት የሚመጥን አደረጃጀት እና ፈፃሚ ባለሙያዎች ይኖሩታል፡፡

## PART TWO

## ESTABLISHMENT OF INSTITUTION

4. **Establishment of Building Construction Permit and Supervision Institution**

1/ In the cities where the Proclamation is to be implemented, a BBuilding Construction Licensing and Supervision Institution shall be established in a manner that may avoid overlap in conformity with the existing arrangement to administer and enforce building permits and supervision, here in after referred to as "Institution".

2/ Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this Article, the name and organization of an institution that conducts building permit and supervision activities may be determined by law on the basis of their own circumstances;

3/ The head of the institution shall be appointed by the head of a building with relevant educational qualification and work experience or by the head of a designated office, depending on the circumstances of the Region, as well as the organization and executives appropriate for his activities.

https://ethiodata.et/

፬/ የህንፃ ሹሙን ወይም ለዚሁ ሀላፊነት የተሰየመው አካል ዝርዝር ተግባርና ኃላፊነት አዋጁን ለማስፈፀም በሚወጣው የህንፃ ደንብ ወይም መመሪያ ወይም በክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች በህግ የሚወሰን ይሆናል፡፡

## ፭.<u>የከተማ ተቋም ተግባር እና ኃላፊነት</u>

ተቋሙ የሚከተሉት ተግባር እና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

፩/ የግንባታ ፈቃድ ለመውሰድ ማመልከቻ ሲቀርብለት ዲዛይኑ ከዚህ አዋጅ፣ ከሌሎች ሕጎች እና በስራ ላይ ያሉ የኢትዮጵያ የህንጻ ስታንዳርዶችን የተከተለ መሆኑን በማረጋገጥና በማፅደቅ የግንባታ ፈቃድ ይሰጣል፤ በግንባታ ሂደት ላይ ያሉ ሕንፃዎች ከዚህ አዋጅ፣ ከሌሎች ሕጎች እና በስራ ላይ ካሉት የኢትዮጵያ የህንጻ ስታንዳርዶች ጋር የሚስማሙ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ቁጥጥር ያደርጋል፤ ባልፀደቀ ዲዛይን መሠረት የሚገነባ ህንፃ የማስቆምና አስጊ ሕንጻ መሆኑ ከተረጋገጠ እንዲፈርስ ያደርጋል፤

፪/ በስህተት በፀደቀ ዲዛይን መሠረት የተገነባ ህንፃ፤ ያፀደቀው አካል በዚህ አዋጅ ወይም ሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጎች

4/ The duties and responsibilities of the building officer or the body designated for this responsibility shall be specified in detail in accordance with the Building Regulations or directives issued to implement the Proclamation or as determined by law by the Regions and City Administrations.

## 5. **<u>Duties and Responsibilities of City Institution</u>**

The Institution shall have the duties and powers:

1/ upon application for a building permit, it shall issue a building permit, certifying that the design complies with this Proclamation, other laws and the current Ethiopian building standards; Shall: Stop a building on the basis of unauthorized design and demolish it if it is proved to be a dangerous building; ensure that buildings under construction are in compliance with this Proclamation, other laws and applicable Ethiopian Building Standards;

2/ a building constructed according to incorrect design; subject to the responsibility of the ratified body under

https://ethiodata.et/

የሚኖረው ተጠያቂነት እንደተጠበቀ ሆኖ እንደየ ስህተቱ ዓይነትና መጠን ተገቢውን የማስተካከያ ስራ እንዲከናወን ያደርጋል፤

፫/ የምድብ "መ" ሕንፃ ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ሲጠናቀቅ በፀደቀለት ዲዛይን መሠረት የተገነባ መሆኑን በማረጋገጥ የህንጻ መጠቀሚያ ፈቃድ ይሰጣል፤

፬/ የግንባታ ማሻሻያና እድሳትን በተመለከተ በህንጻ አዋጁ፣ በሌሎች ሕጎች እና በስራ ላይ ባሉት የኢትዮጵያ የህንጻ ስታንዳርዶች መሠረት መርምሮ ፈቃድ ይሰጣል፤

፭/ ግንባታዎች በጥራት እና በተሰጠው የግንባታ ፈቃድ መሠረት መገንባታቸውን ያረጋግጣል፤ለግንባታው የሚቀርብ ግብዓት ጥራት ይቆጣጠራል፤ እንዲሁም የጥራት ጉደለት ባለባቸው ላይ ህጋዊና ተመጣጣኝ እርምጃ ይወስዳል፤

፮/ በከተማው የአስተዳደር ወሰን ውስጥ የሚገኙ የህንጻ ግንባታዎችን መረጃ አደራጅቶ ይይዛል፤

፯/ የህንጻ ግንባታ ማከናወን የሚፈልጉ ዓለም አቀፍ ዲፕሎማቲክ ተቋማት ከደህንነት ጋር በተገናኘ ከሚመለከተው አካል የትብብር ደብዳቤ ሲያቀርቡ ወይም ለሀገር ደህንነት ሲባል በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ በሚለዩ ህንፃዎች ላይ

this Proclamation or other relevant laws; provides appropriate corrective action according to the type and extent of the error;

3/ a Category "D" building use permit shall be issued upon completion of all or part of the building in accordance with the approved design;

4/ examine and issue licenses in accordance with the Building Proclamation,other laws and applicable Ethiopian Building Standards regarding construction renewals and renovations;

5/ ensures that constructions are constructed in accordance with the quality and construction permit issued; supervises the quality of inputs for construction and takes legal and reasonable action against those who lack quality;

6/ organizes and keep information on buildings within the City Administration;

7/ International diplomats who wish to construct a building shall submit a building permit in writing when they submit a letter of cooperation from the relevant body in relation to security or to buildings designated by the Council of Ministers for national security without

https://ethiodata.et/

የግንባታው ዲዛይን ሳይመረመር የአገልግሎት ክፍያ በማስከፈል የግንባታ ፈቃድ በጹሁፍ ይሰጣል፡፡

**፮.የክልሉ ተቋም ተግባርና ኃላፊነት**

የክልሉ ተቋም ይህን አዋጅ በማስፈጸም ረገድ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖረዋል፡-

፩/ ከከተማ የአስተዳደር ወሰን ውጪ አዋጁ ተፈጻሚ ለሚሆንባቸው አካባቢዎች የሚያስፈጽሙ አካላት ይሰይማል፡፡

፪/ በአቅም ማነስ ወይም በሌላ ምክንያት የሕንፃ ግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ተቋም ወይም ሌላ ተመሳሳይ አደረጃጀት ሊፈጥሩ ባልቻሉ ወይም ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ባለሙያዎች ባልተሟላባቸው ከተሞች የሌላ ከተማ የሕንፃ ግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ተቋም በውክልና አዋጁን እንዲያስፈጽም ይወስናል፤ዝርዝሩ አዋጁን ለማስፈጸም በሚወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

፫/ በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ከተሞች አዋጁን ለመፈጸምና ማስፈጸም እንዲችሉ የአቅም ግንባታና የቴክኒክ ድጋፍ ያደርጋል፡፡

፬/ የከተሞች የሕንፃ ግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ተቋማትን አፈጻጸም ይከታተላል፣ ይፈትሻል፣ክፍተቶችን ይለያል፣ ክፍተቶቹን

examining the design of the building;

**6. Duties and Responsibilities of the Regional Institution**

The Regional Institution shall have the following duties and powers:

1/ It shall appoint the executive bodies for the areas to which the Proclamation is to be implemented outside the jurisdiction of the city.

2/ In cases where unable to organize the building construction permit and supervision institution or other similar organization in cities due to lack of capacity or other reasons or necessary personnel for the work are not available, another city building licensing and supervision institution shall be delegated to implement the Proclamation; the details shall be determined by the Regulation issued to implement this Proclamation;

3/ provide capacity building and technical support to the cities in the Region to implement and enforce this Proclamation;

4/ monitor, inspect, identify gaps, fill in the gaps on the performance of the city's building construction permit and

https://ethiodata.et/

የመሙላት ሥራ ይሠራል፡፡

፭/ ከፍርድ ቤቶች እና ከሌሎች አካላት ለሚቀርቡ ቴክኒክ ነክ ጥያቄዎች ሙያዊ አስተያየት ይሰጣል፡፡

፮/ በህንጻዎች ውስብስብነትና ልዩ ልዩ ባህሪያት በስራቸው ካሉ ከተሞች አቅም በላይ በሆኑ ህንጻዎች ላይ የዲዛይን ማጽደቅ፣ የግንባታ ክትትልና ቁጥጥር ስራዎችን ያከናውናል፡፡

፯/ የህንጻ አዋጁ ተግባራዊ በሚሆንባቸው ከተሞች ከግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ስራዎች ጋር ተያይዞ የሚነሱ ቅሬታዎችን በመመርመር ውሳኔ የሚሰጥ እና ተገቢውን ሙያዊ ስብጥር ያላቸው አባላት የሚገኙበት የይግባኝ ሰሚ ቦርድ በዚህ አዋጅ መሠረት እንዲቋቋም ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፤

፰/ ከዚህ አዋጅ እና አዋጁን ለማስፈጸም ከሚወጡ ሕጋጋት ጋር ሳይቃረኑ በሥራቸው የሚገኙ ከተሞችን ዲዛይን፣ ኮንስትራክሽን፣ የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር እንዲሁም የባለሙያዎችና ድርጅቶች የምዝገባ ፈቃድን በተመለከተ አገልግሎትን ሊያዘምኑ እና ሊያሳልጡ የሚችሉ አዳዲስ ዲጅታል፣ ኦንላይን ቴክኖሎጂዎችን ውስጥ በማስገባት በከተሞቹ ተፈፃሚ የሚሆኑ የዲዛይንና ኮንስትራክሽን ዘዴ መስፈርቶችና መመዘኛዎችን ያወጣል፤፤

supervision institutions;

5/ provides professional advice on technical questions from courts and other bodies ;

6/ Carries out the design approval, construction monitoring and supervision of buildings over the complexity and diversity of buildings;

7/ monitor and support the establishment of an Appellate Board in accordance with this Proclamation, which shall investigate and resolve complaints related to construction permit and inspections in the cities where the Building Proclamation is to be implemented;

8/ Notwithstanding the provisions of this Proclamation and other laws enacted to implement this Proclatation,services related to City design, construction, building permit issuance and supervision, as well as the registration and licensing of professionals and entities may be accomplished through the integration of new digital and online technologies. Accordingly, cities shall issue binding procedures, standards, and guidelines governing design and construction practices.

https://ethiodata.et/

፱/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፮ መሠረት ለከተሞች ባልተሰጡና ክልሎች ራሳቸው በሕግ የሚወሰኑዋቸውን ተጨማሪ ስራዎችንና ተግባራትን የመፈፀም ኃላፊነት ሊኖረው ይችላል፡፡

## ክፍል ሦስት

## ስለፈቃድ አሰጣጥ

### ፯.ጠቅላላ ድንጋጌዎች

፩/ ማንኛውም ሰው አዲስ ግንባታ ለማከናወን ወይም ነባር ህንጻን ለማሻሻል ወይም ለማስፋፋት ወይም ለማፍረስ የአገልግሎት ለውጥ ለማድረግ በቅድሚያ ተገቢውን የግንባታ ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል፡፡

፪/ ማንኛውም ሰው በምድብ 'መ' ሥር የሚመደብ አዲስ የተጠናቀቀ ህንፃ ወይም በከፊል የተጠናቀቀ ህንጻ ወይም የአገልግሎት ለውጥ ወይም ማስፋፋት የተደረገለትን ህንፃ አገልግሎት ላይ ለማዋል በቅድሚያ ተገቢውን የህንጻ መጠቀሚያ ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል፡፡

### ፰.ለአዲስ ግንባታ ፈቃድ ለማግኘት መሟላት ስለሚገባቸው ሁኔታዎች

፩/ማንኛውም ሰው ለአዲስ ግንባታ ፈቃድ ለማግኘት፡-

ሀ) በቅድሚያ ከሚመለከተው አካል የፕላን ስምምነት ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

9/ In accordance with Article 6 of this Proclamation, it may be responsible for carrying out additional works and activities which are not assigned to the cities and which are determined by law.

## PART THREE

## BUILDING PERMIT

### 7. General Provisions

1/ Any person must first obtain the appropriate building permit to carry out a new construction or to upgrade or expand or renovate an existing building.

2/ Any person who has a new finished building or a semi-finished building or a modified or expanded building under Category 'D' must first obtain the appropriate building permit.

### 8. Conditions that must be met to Obtain a Building Permit

1/ Any person to get permission for new construction:

a) First, the relevant party must submit a plan agreement.

https://ethiodata.et/

ለ)የግንባታ ፈቃድ ለማግኘት የሚፈልግ ሰው ለሚገነባው ህንፃ ዲዛይን ማቅረብና ማስፀደቅ አለበት፡፡

፪/ የከተማ ፕላን ባልተዘጋጀላቸው ከተሞች ክልሎች በሚያወጡት ህግ መሠረት የተዘጋጀ የፕላን ስምምነት መቅረብ አለበት፡፡

፫/ ተቋሙ የቀረበለትን የፕላን ስምምነት መሠረት በማድረግ አመልካቹ የግንባታ ፈቃድ ማመልከቻ እንዲያቀርብ በጽሁፍ ያሳውቀዋል፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (፫) መሰረት የግንባታ ፈቃድ ማመልከቻ እንዲያቀርብ በፅሁፍ የተነገረው ሰው ማመልከቻ እንዲያስገባ በተፈቀደለት ጊዜ ውስጥ ማመልከቻውን ማቅረብ አለበት፡፡

፭/ ሕንፃን ለመገንባት የሚቀርብ ማመልከቻ እንደ ሕንፃው ምድብ አይነት ዲዛይንና ሪፖርቱን ያካተተ መሆን ይኖርበታል፡፡ የማመልከቻው ዝርዝር ይዘት ደንብ እና መመሪያ ላይ ይወሰናል፡፡

፮/ ለግንባታ ፈቃድ የሚቀርብ ዲዛይን በህንጻ አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ እንዲሁም በኢትዮጵያ የህንጻ ስታንዳርዶች መሠረት ለሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ተደራሽ ሊሆን በሚችል መልኩ ተዘጋጅቶ ከማመልከቻው ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፡፡

b) The person who wants to get a construction permit must submit and approve the design of the building to be built.

2/ In cities where urban planning has not been prepared, planning agreement prepared according to the laws issued by the Region must be submitted

3/ In writing, the applicant should submit a construction permit application based on the planning agreement provided to the institution;

4/ Application of the person notified in writing to submit a construction permit application based on sub-section 3 of this Article, the application must be submitted within the time allowed for submission.

5/An application to build a building must include a design and report according to the category of the building. The content of the application list depends on the Regulations and Directives.

6/ Design submitted for construction permit according to Building Proclamation, Regulations and guidelines as well as Ethiopian building standards,it should be prepared in a way that is accessible to all sections of the society and should be submitted along with the application.

https://ethiodata.et/

## ፱. ስለ ህንፃ ዲዛይን፣ ዲዛይን መገምገም እና ስለ ማስፀደቅ

፩/ ተቋሙ አንቀጽ ፰ ንዑስአንቀፅ (፮) መሰረት የቀረበለትን ዲዛይን ለማፅደቅ ከዚህ አዋጅ፣ ይህን አዋጅ ለማስፈፀም ከሚወጡት ደንብ፣ መመሪያ እንዲሁም ከኢትዮጵያ የህንጻ ስታንዳርዶች ጋር እና ለሁሉም የማህበረሰብ ክፍል ተደራሽነትን ማረጋገጥ አለበት፡፡

፪/ ተቋሙ የቀረበለትን የህንጻ ዲዛይን ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣው ደንብ በሚወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ መገምገም እና ማጽደቅ አለበት፡፡

፫/ በዚህ አዋጅ ወይም ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ ወይም መመሪያዎች ያልተካተቱ መመዘኛዎችን ምክንያት በማድረግ ዲዛይን እንዳይፀድቅ ማድረግ አይችልም፡፡

፬/ የቀረበው ዲዛይን መሰረታዊ ግድፈት የሌለበት ከሆነ እና ተፈላጊው ማስተካከያ በግንባታ ሂደት በቀላሉ መስተካከል እንደሚችል በታመነበት ጊዜ ተቋሙ አስተያየቱን በማከል ዲዛይኑን ሊያፀድቀው ይችላል፡፡ በዲዛይን ዝግጅት የመሰረታዊ ግድፈት መመዘኛዎችን በተመለከተ በደንብ እና በመመሪያ ይወሰናል፡፡

## 9. About Building Design, Design Review and Approval

1/ From this decree to approve the design submitted to the institute in accordance with Article 8(6), from the Regulations issued to implement this Proclamation, Guidelines as well as Ethiopian Building Standards and ensuring accessibility to all sections of the community.\

2/ The building design submitted to the institution within the time limit determined by the regulations issued to implement this Proclamation.

3/ Reasons for standards not included in this decree or regulations or instructions issued to implement this Proclamation.

4/ If there is no basic omission in the proposed design and the necessary adjustment can be easily adjusted during the construction process. When it is believed to be possible, the institution can approve the design by adding comments. Exclusion criteria are determined by regulations and guidelines.

https://ethiodata.et/

፭/ የፀደቀ ዲዛይን በላዩ ላይ “ፀድቋል” የሚል ማህተም የተደረገበት፣ የምዝገባ ቁጥርና የፀደቀበትን ቀን የያዘና የሚመለከተው ባለሙያ እና የስራ ኃላፊ ፊርማ እንዲሁም የተቋሙ ማህተም ያረፈበት መሆን ይኖርበታል፡፡

፮/ የባለቤትነት ይዞታው ለሌላ አካል ሲዛወር የፀደቀው ዲዛይን ለውጥ ከሌለው በተዛወረው ዲዛይን በላዩ ላይ “ከ……ወደ……ተዛውሯል” የሚል ማህተም የተደረገበት፣የምዝገባ ቁጥርና የተዛወረበትን ቀን የያዘና የሚመለከተው ባለሙያ እና የስራ ኃላፊ ፊርማ እንዲሁም የተቋሙ ማህተም ያረፈበት መሆን አለበት፡፡

፯/ ከተማ አስተዳደሩ በቀጣይ እንደ ሁኔታዉ እየለየ ከአቅም በላይ የሆኑ ስራዎች ወይም አገለግሎቶቸ ሲያጋጥሙ እና አስፈላጊ መሆኑ ሲታመነበት በከፊል ወይም በሙሉ ስራዎች በሌላ አካል እንዲሰሩ ሊፈቅድ ይችላል፡፡ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡

፰/ ማህተምና ፊርማ ያረፈበት የማመልከቻ ቅፅ እና በአባሪነት የተያያዘው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፫/ መሠረት የፀደቀ ዲዛይን ሁለት ቅጅ ለአሰሪው መሰጠት ያለበት ሲሆን፤ ሌላው አንድ ቅጅ ደግሞ በተቋሙ ዘንድ ይቀመጣል፡፡

5/ An approved design stamped “Approved” bearing the registration number and date of approval. It should bear the signature of the concerned professional and official and the seal of the institution.

6/ If the approved design does not change when the ownership is transferred to another party On the transferred design Stamped "Transferred from... to..." bearing registration number and date of transfer and applicable It must bear the signature of the professional and the official and the seal of the institution.

7/The City Council may, as the case may be, permit part or all of the resources available in the event of overwhelming work or services and when it is deemed necessary.The Details may be determined by a Directive.

8/ The application form with seal and signature attached and approved according to sub-article /3/ of this Article two copies of the design must be given to the employer, and the other copy will be kept at the Institution.

https://ethiodata.et/

## ፲.ዲዛይን ውድቅ ስለማድረግ

፩/ ከዚህ አዋጅና ይህን አዋጅ ለማስፈጸም ከሚወጣ ደንብ ወይም መመሪያዎች ጋር የማይጣጣም ዲዛይን ውድቅ ይደረጋል፡፡እንዲሁም ለሁሉም ማህበረሰብ ክፍል ተደራሽ ያልሆነ የህንጻ ምድብ ውድቅ መደረግ ይኖርበታል፡፡

፪/ ዲዛይን ውድቅ የሚሆን ከሆነ ተቋሙ ውድቅ የተደረገበትን ምክንያት በጽሑፍ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

፫/ ውድቅ የተደረገ ማመልከቻና ዲዛይን በእያንዳንዱ ቅጂ ላይ "ውድቅ ተደርጓል" የሚል ምልክትና ቀን እንዲሁም የሚመለከተው ባለሙያ፣የህንፃ ሹሙ ወይም የሚመለከተው ኃላፊ ፊርማ ይሠፍርበታል፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፩ እና ፫ ውድቅ የተደረገ ዲዛይን አንድ ቅጂ በተቋሙ ዘንድ የሚቀመጥ ሲሆን ቀሪው ለአሰሪው የሚመለስ ይሆናል፡

## ፲፩.ዲዛይን ስለማዘዋወር

፩/የፀደቀ ዲዛይን የስም ዝውውር ለውጥ ለማግኘት የሚፈልግ ሰው የሚዘዋወረውን ህንፃ ዲዛይን ማቅረብ አለበት፡፡

## 10. Rejection of Design

1/ Designs that do not comply with this Proclamation and the Regulations or Directive issued to implement this Proclamation shall be rejected.

2/ If the design is rejected, the institution shall notify in writing the reason for the rejection.

3/ Rejected application and design shall be marked on each copy with the mark and date "Rejected" and the signature of the relevant professional or building officer.

4/ A copy of the design rejected in sub-articles 1 and 3 of this Article shall be kept by the institution and the remainder shall be returned to the employer.

## 11.Change of Design Title Deed

1/A person who wants to change the name of approved design must submit the design of the transferring building.

https://ethiodata.et/

፪/የፀደቀ ዲዛይን ስም ማዘዋወርያ ፈቃድ ለማግኘት ቀደም ሲል በህንጻ አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ እንዲሁም በኢትዮጵያ የህንጻ ስታንዳርዶች መሠረት ፀድቆ የተዘጋጀውን ዲዛይን ከማመልከቻው ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፡፡

፫/ ለምድብ "መ" ሕንጻዎች የሚቀርብ የጸደቀ ዲዛይን ስም ማዛወር ጥያቄ በአዋጁ መስፈርት ያለፈ የህዝብ መገልገያ ሕንጻ የአካል ጉዳተኞች ተደራሽነትን ከማረጋገጥ አኳያ ታይተው ለአካል ጉዳተኞች መሟላት ያለበትን የፀደቀ ዲዛይን ከማመልከቻው ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ ፩ እና ፫ መሰረት የተደረገ የዲዛይን ማዘዋወርያ አንድ ቅጂ በተቋሙ የሚቀመጥ ሲሆን ቀሪው ለአሰሪው የሚመለስ ይሆናል፡

**፲፪.** <u>**የግንባታ ፈቃድ ፀንቶ ስለሚቆይበት ጊዜ**</u>

፩/ የግንባታ ሥራው ካልተጀመረ የግንባታ ፈቃዱ ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ የሚያበቃው የግንባታው ፈቃድ ፀድቆ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ እስከ ስድስት ወር ባለው ጊዜ ውስጥ ይሆናል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ ፩ የተደነገገው ቢኖርም እንደ ግንባታው ውስብስብነት እየታየ ክልሉ ወይም የከተማ አስተዳደሩ

2/ In order to obtain an approved design name transfer permit, the design approved in accordance with the Building Proclamation, Regulation, Guidelines and Ethiopian Building Standards must be attached with the application.

3/ In order to obtain an approved design name transfer permit for category "D" buildings shall be accompanied by an application for the approval of a building design for persons with disabilities in order to ensure access to public facilities that exceed the requirements of the Proclamation.

4/ A copy of the design transfer in accordance with sub-articles 1 and 3 of this Article shall be kept by the institution and the rest shall be returned to the employer.

12. <u>**Effective Time of a Construction Permit**</u>

1/ If the construction work does not begin, the validity of the construction permit shall expire within six months from the date of issuance of the construction permit.

2/ If the work is started but the work is not completed, the validity of the construction permit expires from the date of issuance of

https://ethiodata.et/

በሚወጣው ደንብ መሰረት የግንባታ ፍቃዱ የሚቆይበት ጊዜው ሊራዘም ይችላል፡፡ሆኖም የግንባታ ፍቃድ የሚቆይበት ጊዜ፡-

ሀ) ለምድብ "ሀ" ሕንጻ ከሁለት ዓመት፣

ለ) ለምድብ "ለ"ሕንጻ ሶስት ዓመት፣

ሐ) ምድብ "ሐ" ሕንጻ አራት ዓመት እና

መ) ለምድብ "መ" ሕንጻ አምስት ይሆናል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ፩ የተደነገገው ቢኖርም እንደ ግንባታው ውስብስብነት እየታየ ክልሉ ወይም የከተማ አስተዳደሩ በሚወጣው ደንብ መሰረት የግንባታ ፍቃዱ የሚቆይበት ጊዜው ሊራዘም ይችላል፡፡ ሆኖም የግንባታ ፍቃድ የሚቆይበት ጊዜ፡-

ሀ) ለምድብ "ሀ" ሕንጻ ከሁለት ዓመት ከስድስት ወር ፣

ለ) ለምድብ "ለ" ሕንጻ አራት ዓመት

ሐ) ለምድብ "ሐ" ሕንጻ ከአምስት ዓመት

መ) ለምድብ "መ" ሕንጻ ስድስት ዓመት መብለጥ አይችልም፡፡

፬/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ፩ ወይም ፪ በተገለፀው መሠረት የግንባታ ፈቃድ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ ሲያበቃ ጊዜው እንዲራዘም በዚህ አዋጅ መሠረት ዲዛይኑን እንደገና የማፀደቅ ጥያቄ መቅረብ

the permit፡

a) 2 years for category “A” buildings

b) 3 years for category “B” buildings

c)for category "C" buildings, 4 years

d)for category "D" buildings, 5 years

3/ Notwithstanding the provisions of this Article 1, the validity of the construction permit may be extended in accordance with the Regulations issued by the State or the City Administration, depending on the complexity of the construction. However, the duration of the construction permit cannot exceed:

i) 2 years and 6 month for category “A” buildings,

ii) 4 years for category “B” buildings

iii) For category "C" buildings, 5 years.

iv) For category "D" buildings, 6 years.

4/ A request for re-approval of the design shall be made in accordance with this Proclamation in order to extend the period of validity of the construction permit in accordance with sub-article (1) or (2) of this Article.The implementation shall be

https://ethiodata.et/

ይኖርበታል፡፡

**፲፫.ጊዜያዊ ግንባታ**

ማንኛወም ሰው በሕጋዊ ይዞታው ላይ ጊዜያዊ ግንባታ ለመገንባት ማመልከቻ ሲያቀርብ ተቋሙ ሕግና ደንብን የተከተለ ጊዜያዊ ፈቃድ ሊሰጠው ይችላል፡፡ የአፈጻጸሙ ዝርዝር በደንብ እና በመመሪያ ይወሰናል፡፡

**፲፬.የአገልግሎት ለውጥ፣ ማስፋፋት፣ ዕድሳት ወይም ጥገና ስለማድረግ**

፩/ ማንኛውም ሰው ተገቢውን ፈቃድ ሳያገኝ አንድን ነባር ህንጻ የአገልግሎት ለውጥ ማድረግ፣ ማስፋፋት ወይም ማሻሻል፣ ማደስ እና መጠገን አይችልም፡፡

፪/ ማንኛውም ሰው አንድን ነባር ህንጻ የአገልግሎት ለውጥ ማድረግ፣ ማስፋፋት ወይም ማሻሻል፣ ማደስ እና መጠገን ፈቃድ ሲጠይቅ ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ መሆኑን አብሮ መታየት አለበት፡፡

፫/ተቋሙ የአንድን ህንፃ አገልግሎት ለውጥ ለማድረግ፣ ለማስፋፋት ወይም ለማሻሻል፣ ለማደስ ወይም ለመጠገን ፈቃድ አሰጣጥ ዝርዝር አዋጁን ለማስፈጸም በሚወጣው ደንብና መመሪያ

determined in detail by the Regulations and Directives issued for the implementation of this Proclamation.

13. **Temporary Construction**

Any person applying for a temporary building on his legal property may be granted a temporary permit in accordance with the law and Regulations.The implementation shall be determined in detail by the Regulations and Directives issued for the implementation of this Proclamation.

14.**Changing, Expanding, Renovating or Repairing a Building**

1/ Any person changes, expands or improves an existing building without obtaining a proper permit; it cannot be renewed or repaired.

2/ When any person aske for permission to change, expand or improve, renovate and repair an existing building, it should be noted that it is accessible to the disabled.

3/ Permission for the institution to change, expand or improve, renovate and repair a building delivery details will be determined by the Rules and Regulations issued to implement this Proclamation.

https://ethiodata.et/

ይወሰናል፡፡

፬/የአገልግሎት ለውጡ፣ የማስፋፋቱ ወይም የማሻሻሉ፣ የማደሱ እና የመጠገኑ ሥራ ሰፊ የሆነ እንደሆነ ተቋሙ ህንፃው የሚገኝበትን ነባራዊ ሁኔታ የሚያሳዩ ዲዛይኖች በአዋጁ መሠረት መከናወኑን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ማናቸውም ሌሎች ዝርዝር ማስረጃዎች እንዲቀርቡለት መጠየቅ ይችላል፡፡

፭/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ ፪ ድንጋጌ ቢኖርም የታሪካዊ ቅርስነት ዋጋ ያላቸውን ህንፃዎች ለማስፋፋት ወይም ለማሻሻል እንዲሁም ለማደስ ወይም ለመጠገን ወይም ለማፍረስ ሲፈለግ ከሚመለከተው አካል የስራውን ተገቢነት የሚያረጋግጥ የጽሁፍ ስምምነት ማግኘት ይኖርበታል፡፡

## ፲፭.የህንፃ ማፍረስ ፈቃድ ስለመስጠት

ተቋሙ ማንኛውም ህንፃ ለማፍረስ የሚቀርብለትን ጥያቄ አዋጁን እና አዋጁን ተከትሎ ከሚወጣው ደንብና መመሪያዎች ጋር በማገናዘብ የማፍረሻ ፈቃድ ይሰጣል፡፡

## ፲፮. ስለ ህንፃ መጠቀሚያ ፈቃድ

፩/በምድብ ‘መ’ ሥር የሚመደብ አዲስ የተጠናቀቀ ህንፃ ወይም በከፊል የተጠናቀቀ ህንጻ ወይም የአገልግሎት ለውጥ ወይም ማስፋፋት የተደረገለት ህንፃ፣ በህንጻ ሕግጋት የተደነገጉ አስገዳጅ መስፈርቶች እና ዲዛይኑን

4/ If the service change, expansion or improvement, renovation and repair is extensive, the institution building Any other design that can be used to ensure that it is carried out in accordance with the proclamation Detailed evidence may be requested.

5/ In spite of the provision of sub-Article 2 of this Article, to expand or improve the buildings of historical heritage value, also, when it is required to renew or repair or demolish, the relevant party will confirm the appropriateness of the work a written consent must be obtained.

## 15.Issuing a Building Demolition Permit

The institution shall issue a demolition permit in accordance with the Proclamation and the Regulations and Directives issued following this Proclamation.

## 16.About Building Use Permit

1/ A newly completed building under Category `D` or a partially renovated building or a modified or expanded building shall not be used unless a building permit is issued following the mandatory requirements of the Building

ተከትሎ ስለመገንባቱ በማረጋገጥ የመጠቀሚያ ፈቃድ ካልተሰጠው በስተቀር ህንፃው ጥቅም ላይ ሊውል አይችልም፡፡

Code and its design;

፪/ የህንጻ አዋጁ ስራ ላይ ከመዋሉ በፊት የተጠናቀቁና አዋጁ ስራ ላይ ከዋለ በኋላ የተጠናቀቁ የህዝብ መገልገያ ሕንጻ ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ ያልሆነና በአዋጁ መስፈርት ያላለፈ ህንጻ የመጠቀሚያ ፈቃድ ማግኘት አይችልም፡፡ ዝርዝሩ አዋጁን ለማስፈፀም በሚወጣው ደንብና መመሪያ መሠረት ይወሰናል፡፡

2/ Public facilities finished before the Building Proclamation is practical and not qualified according to the Proclamation requirement though finished, concerns the way they can obtain the usage permit having recognized with regard to certifying the accessibility to the disables shall be determined by the Regulation issued to execute the Proclamation.

፫/ ተቋሙ ደህንነቱ አስጊ አለመሆኑ ለተረጋገጠ እና በከፊል ለተጠናቀቀ ህንፃ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚወጣውን ደንብ እና መመሪያ በሚደነግገው መስፈርት መሠረት የጊዜ ገደብን ጨምሮ የመጠቀሚያ ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል፡፡

3/ For a building that is certified as unsafe, the building may be granted a permit for use, including a time limit, in accordance with the requirements of the Regulations and Directives issued for the implementation of this Proclamation.

፬/ በዚህ አዋጅ የተመለከቱት መመዘኛዎች እንደተጠበቁ ሆነው የህንፃ መጠቀሚያ ፈቃድ ተቋሙ የሚሰጥበት የጊዜ ገደብ ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

4/ The time limit set by the Building Use Licensing Institution in accordance with the requirements of this Proclamation shall be met in accordance with the Regulations issued to implement this Proclamation.

፭/ ተቋሙ የህንፃ መጠቀሚያ ፈቃድ ሳይኖረው በምድብ 'መ' ህንፃ መጠቀም በጀመረ በማናቸውም የህንጻ ባለቤት ላይ ሕጋዊ እርምጃ መውሰድ ይችላል፡፡

5/ The institution may take legal action against any building owner who has started using a category `D` building without a building permit.

6/

https://ethiodata.et/

## ክፍል አራት

## ስለ ሕንፃ ግንባታ ክትትልና ቁጥጥር

### ፲፯. የግንባታ መጀመርን ስለማሳወቅ

፩/ በምድብ "ለ" ፣ "ሐ" ወይም "መ" ሥር የሚወድቅ ህንፃ ለመገንባት ፈቃድ የወሰደ ሰው ሥራ ከመጀመሩ በፊት ግንባታው የሚካሄድበትን ጊዜ የሚያሳይ መርሀ ግብር ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት በቀረበ ማስታወቂያ ላይ ተቋሙ የሚሰጠው ውሳኔ የጊዜ ገደብ ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

፫/ ተቋሙ እንደ ህንፃው ዓይነትና የአሠራር ሁኔታ ተጨማሪ ማስታወቂያዎች እንዲቀርቡ መጠየቅ ይችላል፡፡ እንደዚህ አይነት ሁኔታ ሲያጋጥም ማስታወቂያው የሚቀርብበት ጊዜና የሥራው ደረጃ በግልፅ ተቀምጦ ለአመልካቹ ከፀደቀው ዲዛይን ጋር በፅሁፍ እንዲደርሰው ይደረጋል፡፡

፬/ ከፀደቀው ዲዛይን ውጭ የተከናወኑ አንዳንድ ሥራዎችን እንዲያስተካክል ከተቋሙ ትዕዛዝ የደረሰው ሰው የማስተካከያውን ሥራ እንዳጠናቀቀ ለተቋሙ ማስታወቅ ይኖርበታል፡፡

## PART FOUR

## MONITORING AND CONTROL OF BUILDING CONSTRUCTION

### 17. Announcing the Beginning of Construction

1/ A person who is licensed to construct a building under category 'B' or 'C or D shall submit a notice to the institution stating the time of construction before commencement of the work.

2/ The time limit for the decision to be issued in accordance with subarticle (1) of this Article shall be determined by the Regulations issued for the implementation of this Proclamation.

3/The institution may request additional advertisements depending on the type and condition of the building. In such a case, the time and place of the notice shall be clearly stated in writing with the approved design.

4/The person who received the order from the Institute shall notify the Institution that he has completed the repair work in order to correct some work done outside of the approved design.

https://ethiodata.et/

፭/በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ ፩ እስከ ፬ የተደነገገው ቢኖርም ማስታወቂያ ሳይሰጥ የተሰራን ግንባታ በከፊልም ሆነ በሙሉ እንዲፈርስ ወይም እንዲስተካከል ተቋሙ ማዘዝ አለበት፡፡ ዝርዝሩ ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

፲፰. **ስለ ሕንፃ ግንባታ ክትትልና ቁጥጥር**

፩/ ሕጋዊ የግንባታ ፈቃድ አግኝቶ ሥራው በተጀመረ ማንኛውም የሕንጻ ግንባታ ላይ ለግንባታ የሚውሉ ግብዓቶች የጥራት ደረጃቸውን የጠበቁ እና በሚመለከተው አካል የተረጋገጡ ስለመሆናቸው እና ግንባታው የሚካሄድበት ቦታ ደህንነትና ጤንነት አስተማማኝ ለመሆኑ በተቋሙ ክትትልና ቁጥጥር ይደረግበታል፣ ዝርዝሩ ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣው ደንብና መመሪያ ይወሰናል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በየእርከኑ ክትትል ሊደረግባቸው የሚገቡ የግንባታ ስራዎች ሲከናወኑ ክትትልና ቁጥጥር በሚያደርገው አካል ሳይፈቀድ ሥራው ወደፊት መቀጠል አይችልም፡፡

፫/ በግንባታ ሂደት ላይ ያሉ ህንጻዎች በተቀመጡ ኮድና ስታንዳርዶች፣ በዚህ አዋጅና ይህን አዋጅ ተከትለው በሚወጡ ደንብና መመሪያዎች፣ አለማቀፍ አሰራሮችን

5/ Notwithstanding the provisions of sub-article (1-4) of this Article, the institution may order the demolition of a building constructed without proper notice.

18.**Monitoring and Supervision of Building Construction**

1/ The building shall be monitored and supervised by the institution to ensure that the materials used in the construction of the building are of the highest quality and certified by the relevant body and that the construction site is safe and healthy. The details shall be determined by the Regulations and Directives issued for the implementation of this Proclamation.

2/ Without prejudice to the provisions of sub-article 1 of this Article, the construction work to be monitored at all levels shall not be continued without the permission of the supervisory body.

3/ Buildings under construction must be properly monitored to ensure that they are constructed in accordance with the applicable codes and standards, this Proclamation and the Directives and

https://ethiodata.et/

እንዲሁም የአካል ጉዳተኛ ተደራሽነትን አካተው መገንባታቸው በአግባቡ ቁጥጥር ሊደረግባቸው ይገባል፡፡

Guidelines issued pursuant to it, as well as international practices and accessibility requirements for persons with disabilities.

## ፲፱. <u>የተመዘገበ ከፍተኛ የህንጻ ዲዛይን ባለሙያ ስለመቅጠር</u>

፩/ ለማንኛውም ህንፃ ህንፃው በሚገኝበት ምድብ የሚጠየቁ የዲዛይን ዓይነቶች ለግንባታው በሚመጥን በተመዘገበ ከፍተኛ የህንፃ ዲዛይን ባለሙያ መሰራት አለበት፡፡ ዝርዝሩ ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የህንፃ ዲዛይኑን ቴክኒካል ሥራ የሚያስተባብረው አርክቴክቱ ነው፡፡

፫/በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የፕሮጀክት ትግበራ ስራን የማስተባበር ስራ የሚሰራው የህንፃ ዲዛይን ባለሙያው ነው፡፡

፬/የህንፃው ግንባታ እስኪጠናቀቅ ድረስ የቁጥጥር ስራውን የሚያከናውነው የተመዘገበ ከፍተኛ የህንጻ ዲዛይን ባለሙያ የሥራ ተቋራጩን የግንባታ ባለሙያዎችን ይቆጣጠራል፡፡የግንባታ ሥራው ሲጠናቀቅ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /፩/ መሰረት ከፍተኛ የህንጻ ዲዛይን ባለሙያ የፈረመበትና መጠናቀቁን

## 19.<u>Recruitment of Registered Building Design Officer</u>

1/ The design requirements for any building shall be made by a registered consulting firm suitable for the construction.

2/ Notwithstanding the provisions of sub-article (1) of this Article, the Architect shall coordinate the technical work of the building design.

3/ Notwithstanding sub-article 1,of this Article,the building design officer is responsible for coordinating the implementation of the project.

4/ The consulting firm that will carry out the inspection work until the construction of the building is completed should also supervise the construction professionals; Upon completion of the construction work, a certificate signed and certified by the consulting firm referred to in subarticle (1) of this Article shall be submitted to the

https://ethiodata.et/

የሚያረጋግጥ ምስክር ወረቀት ለተቋሙ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

፭/ማንኛውም የምድብ ”ለ” ፣ ”ሐ” እና ”መ” ህንፃዎች ግንባታ ዲዛይን ለማከናወን ውል የሚወስድ የተመዘገበ ከፍተኛ የህንፃ ዲዛይን ባለሙያ በዲዛይን የተነሳ ሊደርሱ ለሚችሉ ጉዳቶች ዋስትና ማቅረብ አለበት፡፡ በየህንፃ ምድቡ የሚያዘው የዋስትና መጠንና አቀራረብ፣ የዋስትና ሰጪ አካላት ሀላፊነት ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

፮/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ እና ፪ ላይ የተጠቀሱት የተመዘገቡ ከፍተኛ የህንፃ ዲዛይን ባለሙያዎች ስራውን በውሉ መሰረት ያስተዳድራሉ፣የተቋራጩን የሰው ኃይል ተገቢውን የግንባታ ግብዓት ጥራት እና አጠቃላይ የሥራውን ጥራት ፕሮጅክቱ እስኪጠናቀቅ ድረስ ይቆጣጠራሉ። የግንባታ ሥራው ሲጠናቀቅ ባለሙያው የፈረመበት መጠናቀቁን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት ለተቋሙ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

## ፳.የተመዘገቡ የሥራ ተቋራጮችን ስለመቅጠር

፩/ ህንፃ ለመገንባት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ለሚገነባው ህንፃ ምድብ የሚመጥን የተመዘገበ ሥራ ተቋራጭ መቅጠር አለበት፡፡ ዝርዝሩ ይህን አዋጅ ለማስፈፀም

institution.

5/ The relevant registered senior building professional referred to in sub-articles 1 and 2 of this Article shall manage the work in accordance with the contract and supervise the contractor's workforce for the quality of the appropriate construction input and the overall quality of the work until the project is completed. Upon completion of the construction work, a registered senior building professional must submit to the institution a certificate confirming the completion of the signing.

6/ Any registered senior building professional who is contracted to carry out the design of the construction of categories 'B', 'C' and 'D' buildings shall provide insurance for damages that may arise as a result of the design.The amount and approach of the securities in each category of buildings, the responsibility of the guarantors shall be determined by the Regulations issued for the implementation of this Proclamation.

## 20.**Recruitment of Registered Contractors**

1/ Anyone wishing to construct a building must hire a registered contractor who is suitable for the category of building to be constructed.The details shall be

https://ethiodata.et/

በሚወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

፪/ ማንኛውም የምድብ ‘ለ’ እና ‘ሐ’ ህንፃዎች ግንባታ ለማከናወን ውለታ የሚወስድ ሥራ ተቋራጭ ግንባታውን በሚያከናውንበት ወቅት በግንባታው የሥራ ጥራትና በጥንቃቄ ጉድለ ት ምክንያት ሊደርስ ለሚችል ጉዳት ለማካካስ የሚረዳ ዋስትና ማቅረብ አለበት፡፡ ዝርዝሩ ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

## ክፍል አምስት

## የመሬት አጠቃቀም፣ ተጓዳኝ ጥናቶች እና የህንፃ ዲዛይኖች

### ፳፩. የመሬት አጠቃቀምና ተጓዳኝ ጥናቶች

በፌዴራል፣በክልል ወይም በከተማ አስተዳደር የፀደቀ አገራዊ፣ክልላዊ ወይም ከተማ ነክ አጠቃላይ ፕላን በዚህ አዋጅ በተካተቱና የመሬት አጠቃቀምንና ተጓዳኝ ጥናቶችን በሚመለከቱ ድንጋጌዎች ላይ የበላይነት ይኖረዋል፡፡

### ፳፪. ለህንፃ ግንባታ መዘጋጀት ስለሚኖርበት ዲዛይን

፩/ ማንኛውም ግንባታ የከተማውን መሪ ፕላን ተከትሎ በሚገኝበት የህንፃ ምድብ የህንጻውን ውስብስብነት እና እንዲሰጥ የታሰበውን አገልግሎት ያገናዘበ ዲዛይን መዘጋጀት አለበት፡፡

determined by the Regulations issued for the implementation of this Proclamation.

2/ Any contractor who is awarded a contract for the construction of Category "B" and C buildings shall provide compensation for the damage caused by the quality of the construction work and the lack of care during the construction. The details shall be determined by the Regulations issued for the implementation of this Proclamation.

## PART FIVE

## LAND USE, RELATED STUDIES AND BUILDING DESIGNS

### 21. Land Use And Related Studies

A national, regional, or city-wide general plan approved by the federal, state, or city administration shall prevail over the provisions of this Proclamation relating to land use and related studies.

### 22. About The Design To Be Prepared For Building Construction

1/ Any construction should follow the city master plan to give the complexity of the building in the building category. It should be designed with the intended service in mind.

https://ethiodata.et/

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ የተጠቀሰው እንዳለ ሆኖ ማንኛውም አሰሪ ለዲዛይን ዝግጅት ትክክለኛ ባለሙያ እና በቂ ጊዜ መመደቡን ማረጋገጥ ያለበት ሲሆን ባለሙያው ለግንባታ በሚያዘጋጀው የዲዛይን ሰነድ በቂ ጊዜ ወስዶ ለግንባታው የሚያስፈልጉ አጠቃላይ የዲዛይን ዝርዝር ይዘቶች የተካተቱ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት።

፫/ ማንኛውም ህንፃ ወይም የህንፃ አካል ተቀባይነት ባላቸው የኢትዮጵያ የህንፃ ስታንዳርዶች መሠረት የተጠቃሚውንም ሆነ የሌሎች አካላትን ደህንነት፣ምቾትንና የተሟላ አገልግሎትን ሊያረጋግጥ የሚችል ሆኖ ዲዛይን መደረግ አለበት፡፡

፬/ ማንኛውም ህንፃ የሰዎችን፣የሌሎች ግንባታዎ ችንና ንብረቶችን ደህንነት በማያሰጋ መንገድ ዲዛይን መደረግ አለበት፡፡

፭/ ማንኛውም ህንጻ በሚገኝበት ምድብ መስፈርት መሰረት አርክቴክቸራል፣ስትራክቸ ራል፣ ሳኒተሪ፣ ኤሌክትሪካል፣ መካኒካል እና የኤሌክትሮ ሜካኒካል እንዲሁም ሌሎች መሰ ረታዊ ዲዛይኖችን ጨምሮ እንደአካባቢው ሁኔ ታ የሚመለከታቸው መንግስታዊ አካላት በሚያወጡት የልዩ ፍላጎት መስፈርቶችን በማካተት ማዘጋጀት አለበት፡፡

2/ Notwithstanding the provisions of sub-article 1 of this Article, any employer shall ensure that proper professional and sufficient time is allocated for design preparation, and that the professionals shall take sufficient time in the design documents prepared for construction and include the contents of the entire design specifications required for the construction.

3/ Any building or part of a building that is acceptable according to Ethiopian building standards and the user's It should be designed in such a way as to ensure safety, comfort and complete service of other parts.

4/ Any building should be designed in a way that does not threaten the safety of people, other buildings and property.

5/ Any building shall be prepared according to the criteria of the category in which it is located,including architectural, structural, sanitary, electrical, mechanical and electro-mechanical, as well as other basic designs, according to the requirements of the special needs issued by the relevant governmental bodies according to local conditions.

https://ethiodata.et/

፮/ በምድብ "መ" ስር ያሉ የሕንጻ ዲዛይኖች ሲዘጋጁ አማራጭ የሃይል አቅርቦትን (ታዳሽ ኃይሎችን) መጠቀም እንዲያስችል ታሳቢ ተደርገው መዘጋጀት አለበት:: ዝርዝሩ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣው ደንብና መመሪያ ይገለፃል፡፡

6/ To enable the use of alternative energy supply (renewable energy) when building designs are prepared the details to be consideredand prepared will be specified in the regulations and instructions issued to implement this Proclamation.

፯/በምድብ "መ" ስር ያሉ የሕንጻ ዲዛይኖች ሲዘጋጁ የአረንጓዴ ኮንስትራክሽንን እንዲያበረታቱ ታሳቢ አድርጎ መዘጋጀት አለበት፡፡ዝርዝሩ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣው ደንብና መመሪያ ይገለጻል፡፡

7/ When preparing the building designs under category "D", it should be prepared with consideration to encourage green construction. The details shall be specified in the Regulations and Directives issued to implement this decree.

፰/ማናቸውም የህንፃ ዲዛይን በሚዘጋጅበት ወቅት ዲዛይኑን የሚያዘጋጀው ባለሙያ ዘመኑ የደረሰበትን ቴክኖሎጂ፣የአረንጓዴ ልማትን ታዳሽ ሀይልን በቁጠባ መጠቀም የሚያስችል እና ዘለቄታ ልማትን ታሳቢ በማድረግ ማዘጋጀት ይኖርበታል፡፡ዝርዝሩ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣው ደንብና መመሪያ ይገለጻል፡፡

8/ Whenever a building design is being prepared, the professional responsible for the design is expected to incorporate contemporary technology, consider green development and efficient use of renewable energy,and promote sustainable development in the preparation process. The details of this requirement will be outlined in a Regulation and Directive to be issued for the implementation of this Proclamation.

፱/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፬ መሠረት የሚዘጋጁ አርክቴክቸራል፣ ስትራክቸራል፣ ሳኒተሪ፣ ኤሌክትሪካል እና የኤሌክትሮ ሜካኒካል ዲዛይኖች ሊያሟሉት የሚገባቸውን መስፈርቶች በተመለከተ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣው ደንብ

9/" Pursuant to Sub-Article 4 of this Article, the standards required for the preparation of architectural, structural, sanitary, electrical, and electro-mechanical designs shall be prescribed by a Regulation and Directive to be issued for the implementation of this

https://ethiodata.et/

እና መመሪያ ይወሰናል፡፡

Proclamation.

## ፳፫. የአካል ጉዳተኞች ተደራሽነት

## 23.Accessibility to the Disabled

፩/ማንኛውም የህዝብ መገልገያ ህንጻ ዲዛይን በሚዘጋጅበት ወቅት ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ እና ምቹ በሆነ መልኩ ሁሉን አቀፍ ዲዛይን ተከትሎ መዘጋጀት አለበት፡፡

1/During the design of any public utility building, it must be designed following a comprehensive design in a manner that is accessible and convenient to use for persons with disabilities and members of the public who need special attention.

፪/ በምድብ "መ" ስር የሚገኝ ማንኛውም ነባር የህዝብ መገልገያ ህንጻዎች ባሉበት ሁኔታ ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ መደረግ አለባቸው፡፡ ዝርዝሩን በተመለከተ አዋጁን ለማስፈፀም በሚወጣው ደንብና መመሪያ ይወሰናል፡፡

2/Any existing public utility buildings under category "D" shall be made accessible in a manner that ensures convenience for persons with disabilities and those in need of special attention.

## ፳፬.ዲዛይን ለመገምገም፣ ለማፀደቅና ለቁጥጥር ስለሚፈጸም ክፍያ

## 24. Payment for Design Review, Approval and Inspection

፩/ ዲዛይንና ሌሎች ሰነዶች ለማጸደቅ የዲዛይን መገምገሚያ ወይም ማጽደቂያ ክፍያ ይከፈላል፡፡

1/ Design review or approval fee shall be paid upon request for design and other documents.

፪/ ለቁጥጥር ሲባል ለሚደረግ ጉብኝት የህንፃውን ምድብ መሠረት ያደረገ የቁጥጥር ክፍያ መከፈል አለበት፡፡ ዲዛይን ለመገምገም፣ ለማፀደቅና ለቁጥጥር የሚፈጸመው የክፍያ መጠን ይህን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

2/ An inspection fee based on the category of the building must be paid for an inspection visit. The amount to be paid for the evaluation, approval and inspection of a design shall be determined by a Regulation issued for the implementation of this Proclamation.

https://ethiodata.et/

፫/ ማንኛውም አገልግሎት ያልተሰጠበት ክፍያ ከአመልካች በሚቀርብ የፅሁፍ ጥያቄ አግባብነት ባላቸው የፋይናንስ ህጎች መሠረት ተቋሙ ተመላሽ እንዲሆን ማዘዝ ይችላል፡፡

3/Any unpaid service may be ordered to be refunded in accordance with the relevant financial laws at the request of the applicant.

## ክፍል ስድስት

## የግንባታ ደህንነት እና የጥንቃቄ እርምጃዎች

### ፳፭.በግንባታ ሂደት መደረግ ስለሚገባቸው ጥንቃቄዎች

፩/ ማንኛውም ግንባታ (አዲስ ህንፃ ግንባታ፣ የነባር ህንፃ ማስፋፊያ ወይም እድሳት እንዲሁም ህንፃ ሲፈርስ) የደህንነትና የጥንቃቄ መስፈርቶችን በሚያረጋግጥ ሁኔታ መፈጸም ይኖርበታል፡፡ በግንባታ ወቅት መወሰድ ስለሚገባቸው የደህንነትና ጥንቃቄ እርምጃዎች እና ስለሚኖር ኃላፊነት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣው ደንብና መመሪያ ይወሰናል፡፡

፪/ ማንኛውም ህንፃ ሲገነባ ወይም ሲፈርስ በሕዝብ ላይ አደጋ ወይም ከፍተኛ መጉላላት ሊያስከትል የሚችል ከሆነ የግንባታ ወይም የማፍረስ ስራ ከመጀመሩ በፊት አሰሪው አስፈላጊውን የጉዳት መከላከያ አጥር ወይም ሌላ መከለያ እንዲሰራ ተቋሙ ሊያስገድደው ይችላል፡፡

## PART SIX

## CONSTRUCTION SAFETY AND SECURITY MEASURES

### 25. Precautions to be taken during the Construction Process

1/ The construction of any new building, expansion or renovation of an existing building as well as in case of demolition should be executed in the way to ascertain the safety and security requirements. The details shall be determined by the Regulations and Directives issued to implement this Proclamation.

2/ If any building is constructed or demolished which may cause danger or great inconvenience to the public, the Institution may compel the employer to erect the necessary protective fence or other shelter prior to the commencement of construction or demolition work.

https://ethiodata.et/

፫/ አንድን ህንፃ ከመገንባት ወይም ከማፍረስ ጋር በተያያዘ በአጎራባች ወይም በቅርበት በሚገኝ ንብረት አጠቃላይ የጥንካሬ፣ የደረጃ፣ የደህንነት፣የጥራት ወይም የአቀማመጥ ሁኔታ ጉልህ ለውጥ የሚያመጣ ተፅዕኖ እንደሚያስከትል ከታመነበት አሰሪው በግንባታ ሥራው ምክንያት ለሚያደርሰው ጉዳት ማካካሻ የሚሆን ማስያዣ ወይም ዋስትና እንዲሰጥ ተቋሙ ሊያስገድደው ይችላል፡፡

3/ If the building construction and demolition is deemed to have a significant impact on the overall strength, status, safety, quality, or layout of a building or its adjacent property, the employer may request or comply with a bond or guarantee for compensation for damages caused by the construction work.

፬/ ማንኛውም ግንባታ ሲከናወን በአካባቢው የሚንቀሳቀሱ ሰዎችን፣ የግንባታውን ሠራተኞችና የሌሎች ንብረቶችን ደህንነት በማያሰጋ መንገድ መገንባት ይኖርበታል፡፡

4/ All construction shall be carried out in a manner that does not endanger the safety of the people moving around, the construction workers and other property;

፭/ ከግንባታ ጋር የተያያዘ የቁፋሮ ስራ የማንኛውንም ንብረት ወይም አገልግሎት ደህንነት አደጋ ላይ ሊጥል የሚችል መሆኑ ሲገመት አሰሪው በቅድሚያ የመከላከያ ዘዴዎችንና የጥንቃቄ እርምጃዎችን ለተቋሙ በማቅረብ የፅሁፍ ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡

5/ The construction site owner must first obtain written permission from the construction company to provide preventive measures and precautionary measures when it is deemed to be endangering the safety of any property or service.

፮/ ማንኛውም አዲስ የሚገነባ ህንፃ የመሠረት ስራው ጭነት በዙሪያው ባሉ ህንጻዎች ላይ እና የአገልግሎት መስመሮች ወይም ሌሎች ሥራዎች ላይ ጉዳት እና በእንቅስቃሴ ላይ ችግር የሚፈጥር መሆን የለበትም፡፡

6/ The foundation load of any new building shall not be a nuisance to the surrounding buildings and service lines or other works.

https://ethiodata.et/

፯/ ተቋሙ በግንባታ ወቅት ሊወሰዱ የሚገባቸውን የጥንቃቄ ስራዎችን ለመከታተል የሚያስችሉ የአሠራር መስፈርቶች ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ፳፮. በግንባታ ቦታ ላይ ስለሚከናወኑ ሥራዎች

፩/ ማንኛውም አሰሪ ከህንፃ ግንባታ ወይም ማፍረስ ጋር የተያያዘ ሥራ የሚሰሩ ሰዎች ሥራውን በሚያከናውኑበት ጊዜ በሥራው ቦታ ላይ እንደ አስፈላጊነቱ ጊዜያዊ መጠለያ እንዲሠራ ሊታዘዝ ይችላል፡፡

፪/ ህንፃ ሲገነባ ወይም ሲፈርስ በሕዝብ ላይ አደጋ ወይም ከፍተኛ መጉላላት ሊያስከትል የሚችል ከሆነ የግንባታ ወይም የማፍረስ ስራ ከመጀመሩ በፊት አሰሪው አስፈላጊውን የጉዳት መከላከያ አጥር ወይም ሌላ መከለያ መስራት አለበት፡፡

፫/ ማንኛውም አሰሪ የህንፃ ግንባታ ወይም የማፍረስ ስራ በሚያከናውንበት ጊዜ በሥራው ላይ ለሚሰማሩ ሰዎች የሚሆን ተቀባይነት ያለው የንጽህና ቦታ በግንባታ ሥፍራው ላይ ወይም በሌላ ቦታ ላይ ሳያዘጋጅ የግንባታም ሆነ የማፍረስ ሥራውን መጀመር አይችልም፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ የተጠቀሰው የዝግጅት ሥራ እስከሚጠናቀቅ ድረስ ሥራው እንዲቆም ተቋሙ ትእዛዝ ሊሰጥ

7/ The institution may issue procedures to monitor the precautionary measures to be taken during construction Process.

## 26. Works On Construction Site

1/ Any building owner may be required to provide temporary accommodation at the site of work during the construction of the building or demolition work.

2/ No employer may commence construction or demolition work without setting up an acceptable sanitary area at the construction site or elsewhere for persons engaged in the work while carrying out building construction or demolition work

3/ No construction site owner or construction worker may start construction or demolition work without a suitable sanitary location at the construction site or elsewhere before construction or demolition work.

4/ The Institution may order to cease the work until the completion of the preparatory work referred to in sub-article

https://ethiodata.et/

ይችላል፡፡

## ፳፯.የግንባታ ቁሳቁሶች እና ተረፈ ግንባታ አያያዝ

፩/ ማንኛውም አሰሪ ግንባታውን ከሚያከናውንበት ይዞታ ውጭ በተለይም በመተላለፊያ መንገዶች ላይ የግንባታ ግብዓትም ሆነ ተረፈ ግንባታ ማከማቸት አይችልም፡፡

፪/ ማንኛውም አሰሪ ከግንባታ ቦታ ክልል ውጪ የግንባታ ቁሳቁስ ወይም ተረፈ ግንባታ ያስቀመጠ ወይም ያጠራቀመ ከሆነ በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ እንዲያነሳ ተቋሙ የጽሑፍ ማስታወቂያ ይሰጠዋል፡፡

፫/ አሰሪው በተሰጠው ማስታወቂያ መሰረት አስፈላጊውን ማስተካከያ ካልፈፀመ ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣው ደንብ መሰረት አስተዳደራዊ እርምጃ ይወሰድበታል፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /"፩/ የተደነገገው ቢኖርም ማንኛውም አሰሪ ከግንባታ ቦታ ክልል ውጪ የግንባታ ቁሳቁስ ወይም ተረፈ ግንባታ ማሰቀመጥ ሲፈልግ ተቋሙ መፍቀድ አለበት፡፡ ዝርዝሩ ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣው ደንብና መመሪያ ይወሰናል፡፡

2 of this Article.

## 27. Handling of Construction Materials and Scrap

1/ No employer shall stockpile any construction materials or surplus construction outside of the construction site.

2/ If any employer has accumulated construction materials or surplus materials outside the construction site, the institution shall give written notice to it within a specified period of time.

3/ If the employer does not make the necessary adjustments in accordance with the notice, administrative action shall be taken in accordance with the Regulations issued to implement this Proclamation.

4/ Notwithstanding the provisions of sub-article /1/ of this Article, any employer who wishes to store construction materials or surplus materials outside the construction site shall be permitted by the institution.The details shall be determined by the Regulations and Directives issued for the implementation of this Proclamation.

https://ethiodata.et/

## ክፍል ሰባት

## የውሃ አቅርቦት፣ ንፅህና አጠባበቅና የቆሻሻ አወጋገድ

## PART SEVEN

## WATER SUPPLY, SANITATION AND WASTE DISPOSAL

**፳፰.የውሃ አቅርቦት**

፩/ማንኛውም ህንፃ እንዲሰጥ የታሰበውን አገልግሎት ያገናዘበ በቂ የውሃ አቅርቦት ሊኖረው የሚገባ ሲሆን የውሃ አቅርቦት ዝግጅቱም በቂ ሥርጭት እና የማከማቻ ዘዴ ማካተት አለበት፡፡

፪/ የማንኛውም ህንፃ የውሃ አቅርቦት ዘዴ የጤና ደረጃውን የጠበቀና የውሃ አቅርቦት አሠራሩም ለምርመራና ለሙከራ የሚመች መሆን ይኖርበታል፡፡

28. **Water Supply**

1/ Every building should have adequate water supply considering the intended service and the water supply arrangement should include adequate distribution and storage system.

2/ The water supply system of any building shall be in accordance with the health standards and the water supply system shall be suitable for inspection and testing.

**፳፱. የፍሳሽ አወጋገድ**

፩/በህንፃ ግንባታው አቅራቢያ ተስማሚ የሆነ የፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ መስመር ሲኖር የህንፃው ባለቤት የፍሳሽ መተላለፊያ በማዘጋጀት ወደዚሁ የቆሻሻ ማስወገጃ ስርዓት ማገናኘት ይኖርበታል፡፡

፪/ ማንኛውም ሰው በአቅራቢያው ተስማሚ የሆነ የፍሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ከሌለው ተቀባይነት ባለው ሌላ መንገድ ፍሳሹን ማስወገድ ይኖርበታል፡፡

29. **Sewage Disposal**

1/ When there is a suitable sewer line near the construction site, the owner of the building should prepare a sewer and connect it to this sewer system.

2/ If anyone does not have a suitable sewer nearby, they should dispose of it in another acceptable way.

**፴.ተቀባይነት የሌላቸውን ፍሳሾች መቆጣጠር**

ማንኛውም አሰሪ ከመፀዳጃ ወይም ከማብሰያ አገልግሎት መስጫዎች የሚወጣን ፍሳሽ

30. **Controlling unacceptable Sewers**

No owner shall allow sewage from sewers or septic tanks to be dumped into any flood

ቆሻሻ ወደ ማንኛውም የጎርፍ ማስወገጃ ቦይ ወይም በሌላ መልኩ ወደ ተገነባ የውሃ መስመር፣ ወንዝ፣ ምንጭ፣ ጎዳና ወይም ሌላ ስፍራ መልቀቅ ወይም እንዲለቀቅ መፍቀድ የለበትም፡፡

drainage canal or other constructed water line, river, spring, street or other location.

## ፴፩.የኢንዱስትሪ ዝቃጭ

፩/ ማንኛውም የህንጻ ግንባታ ባለቤት ፈቃድ ሳይሰጠው የኢንደስትሪ ዝቃጭ ያዘለ ፈሳሽ ወይም ጠጣር ነገር ወደ ማንኛውም ፍሳሽ ማስወገጃ፣ ወንዝ ወይም ደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ መልቀቅ ወይም መጣል አይችልም፡፡

፪/ ለኢንደስትሪዎች ወይም ለፋብሪካዎች አገልግሎት ከሚውሉ ህንጻዎች የሚወጡ ዝቃጮች ብክለትን እንዳያስከትሉ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ሊዘጋጅላቸው እና ግምገማውም በሚመለከተው አካል መፅደቅ ይኖርበታል፡፡

## 31. Industrial Sediment

1/ Any building owner shall not discharge, release, or cause to be discharged or released any industrial waste, toxic fluid, or hazardous substance into any sewage system, river, or dry waste disposal site without obtaining prior permission to do so.

2/ An environmental impact assessment shall be prepared and approved by the relevant body to ensure that the sediments emitted from industrial or factory buildings do not cause pollution.

## ፴፪.ውሀ አልባ ቆሻሻ ማስወገጃ

በውሃ አማካኝነት ቆሻሻ የማስወገጃ ግንባታ በሌለበት ቦታ ሌሎች ቆሻሻ ማስወገጃ ዘዴዎች ጥቅም ላይ እንዲውሉ ተቋሙ ሊፈቅድ ይችላል፤ ሆኖም ኬሚካል ወይም ዝግ ቆሻሻ ማስወገጃ በሚኖርበት ጊዜ ቆሻሻውን ከዕቃው ለማስወገድ ተቀባይነት ያለው ዘዴ ሊኖር ይገባል፡፡

## 32.Waterless Waste Disposal

Where there is no waste disposal facility with water, the facility may allow the use of other waste disposal methods; However, when there is a chemical or closed waste disposal, there must be an acceptable method of disposing of the waste.

https://ethiodata.et/

## ፴፫.የጎርፍ ውሃ ወይም የዝናብ ውሀ ስለማስወገድ

፩/የማንኛውም ህንጻ ባለቤት በማናቸውም ምክንያት ተጠራቅሞ ከይዞታው የሚፈሰውን የዝናብ ውሃ የአጎራባቹን ንብረት ደህንነት በማይጎዳ እና ተቀባይነት ባለው ዘዴ መቆጣጠርና ማስወገድ ይኖርበታል፡፡

፪/ የማንኛውም ይዞታ ባለቤት ከዝናብ ውሃ የተወሰነው በይዞታው ውስጥ ሰርጎ እንዲቀር ተስማሚ ዘዴ መጠቀም አለበት፡፡

## ፴፬.የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ

የመኖሪያ ቤትን ሳይጨምር ደረቅ ቆሻሻ የሚያመነጭ ማንኛውም ህንጻ ወይም ግንባታ የደረቅ ቆሻሻ የሚቀመጥበት በቂ ማከማቻ ቦታ ሊኖረው ይገባል፡፡

## ክፍል ስምንት
## እሳት መከላከል እና የእሳት ማጥፊያ ተከላ

## ፴፭.ጠቅላላ ድንጋጌ

ማንኛውም የህዝብ መገልገያ ህንፃ በኢትዮጵያ የህንፃ ስታንዳርድ እና ሌሎች ተቀባይነት ያላቸው የእሳት

## 33.Flooding Or Disposal Of Rain water

1/ The owner of any building shall control and dispose of rainwater runoff for any reason in a manner that does not harm the safety of the property of the neighbors and in an acceptable manner.

2/ The owner of any property must use appropriate means some of the rainwater to enter underground in order to protect the water level. The details shall be determined by the Regulations and Directives issued for the implementation of this Proclamation.

## 34. Solid Waste Disposal

Any construction that produces solid waste, including housing, should have enough space to store solid waste.

## PART EIGHT
## FIRE FIGHTING AND FIRE EXTINGUISHER INSTALLATION

## 35. GENERAL PRINCIPLES

Every public utility building must be designed and constructed in a manner that is fire resistant and in the event of a fire in

https://ethiodata.et/

መከላከያ ዲዛይን መስፈርቶች መሠረት የእሳት አደጋን ሊቋቋምና የእሳት አደጋ ቢከሰት በተጠቃሚዎችና በአካባቢው ላይ የሚያደርሰውን አደጋ ሊቀንስ በሚችል መልክ ዲዛይን መደረግና መገንባት አለበት፡፡

**፴፮.<u>የእሣት ማጥፊያ መሣሪያ ተከላ</u>**

፩/የእሳት ማጥፊያ መሣሪያ ተከላ እና ገጠማ ከሚመለከተው መንግስታዊ ተቋም የሙያ የምስክር ወረቀት በተሰጠው ሰው ወይም ድርጅት መከናወን አለበት፡፡

፪/በህንጻ ላይ የሚገጠም የእሳት ማጥፊያ መሣሪያ ደረጃውን የጠበቀ ስለመሆኑ የሚመለከተው መንግስታዊ ተቋም ወይም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት የምስክር ወረቀት በተሰጠው ሰው የተረጋገጠ እንዲሁም ስለአስተማማኝነቱ በየጊዜው ፍተሻ የሚደረግለት መሆን አለበት፡፡

፫/ በሕዝብ መገልገያ ሕንፃ ውስጥ የሚገጠም የእሳት ማጥፊያ መሳሪያ በማንኛውም ጊዜ ለአጠቃቀም ዝግጁ መሆን አለበት፡፡

**፴፯.<u>የእሳት መከላከያ የውሃ አቅርቦት</u>**

ለማንኛውም የእሳት ማጥፊያ የሚውል የውሃ መስመር ዝርጋታ የእሳት መከላከያ መሣሪያውና የውሃ አጠቃቀም ከከተማው አስተዳደር መስፈርት ጋር የሚስማማ መሆኑ

accordance with the Ethiopian Building Standards and other accepted fire safety design requirements.

36. **<u>Installation of Fire Extinguisher</u>**

1/ the installation of a fire extinguisher must be carried out by a person or organization who has having a professional certificate from the relevant governmental institution.

2/ A fire extinguisher to be installed on a building shall be certified by the relevant governmental institution or by a person who has been certified in accordance with sub-article 1 of this Article and shall be regularly checked for its reliability

3/ A Fire Extinguisher installed in a public utility building must be ready for use at any time.

37. **<u>Fire Fighting Water Supply</u>**

The water pipe line installation to be used for any fire extinguisher, the firefighting equipment and the water usage shall not be constructed unless certified to be in accordance with the requirements of the city

https://ethiodata.et/

ካልተረጋገጠ እና ለከተማው አስተዳደር በቅድሚያ ማመልከቻ ቀርቦ ፈቃድ ካላገኘ በስተቀር ሊከናወን አይችልም፡፡

administration and approved having applications lodged in advance to the city administration.

## ክፍል ዘጠኝ
## አስተዳደራዊ እና የወንጀል ቅጣቶች

## PART NINE
## ADMINISTRATIVE AND CRIMINAL PENALTIES

### ፴፰.ጠቅላላ ድንጋጌዎች

፩/ ተቋሙ የዚህን አዋጅና አዋጁን ለማስፈጸም የሚወጡ ድንጋጌዎች በሚተላለፉ ሰው ላይ አስተዳደራዊ እርምጃ ሊወስድ ይችላል፡፡ዝርዝሩ ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣው ደንብና መመሪያ ይወሰናል፡፡

፪/ አንድን ድርጊት መፈጸም ወይም አለመፈፀም አስተዳደራዊ ቅጣት እና የወንጀል ኃላፊነት የሚያስከትል በሚሆንበት ጊዜ ጥፋቱን የፈጸመው ሰው አስተዳደራዊ ቅጣት መቀጣቱ የወንጀል ተጠያቂነቱን አያስቀርም፡፡

### 38. GENERAL PROVISION

1/ The Institution may take administrative action against the person who violates the provisions of this Proclamation,.The details shall be determined by the Regulations and Directives issued for the implementation of this Proclamation.

2/ When the act or omission of an act carries an administrative penalty and criminal liability, the administrative punishment of the offender does not preclude criminal liability.

### ፴፱ አስተዳደራዊ ድንጋጌዎች

፩/ ተቋሙ የፀደቀ የሕንጻ ዲዛይን ሳይኖር የተገነባን አዲስ ህንጻ ወይም ማሻሻያ የተደረገበትን ነባር ሕንፃ እንዲፈርስ ወይም እንዲስተካከል ማዘዝ ወይም ግንባታው እንዲቆም ማገድ አለበት፡፡

፪/ በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ "፩" የተገለጸ ቢኖርም ትዕዛዝ ለተላለፈበት

### 39.Administrative Provisions

1/ The institution must order the demolition or modification of a newly constructed building or a renovated existing building that was built without an approved architectural design, or it must suspend the construction.

2/ Notwithstanding the provision of Sub-Article '1' of this Article, if the builder of the

https://ethiodata.et/

ሕንፃ አሰሪው በአዲስ መልክ ዲዛይን አሰርቶ ካቀረበ እና የቀረበው ዲዛይን ከዚህ አዋጅ እና የኢትዮጵያ የህንፃ ስታንዳርድ ግዴታዎች ጋር የተጣጣመ ከሆነ ተቋሙ ዲዛይኑን በማፅደቅ እና አሰሪው ተገቢውን መቀጮ እንዲከፍል በማድረግ ግንባታው እንዲቀጥል ይፈቅድለታል፡፡

building for which a demolition or modification order was issued submits a new design, and if the submitted design complies with this Proclamation and with the mandatory Ethiopian Building Standards, the Institution shall approve the new design and allow the builder to continue the construction upon payment of the appropriate penalty.

፫/ የፀደቀ ዲዛይን ቢኖርም ዲዛይኑን ባለመከተል መሰረታዊ ልዩነት በሚያመጣ አኳኋን የተገነባን አዲስ ግንባታ ወይም ማሻሻያ የተደረገበትን ነባር ሕንፃ ተቋሙ እንዲፈርስ ወይም እንዲስተካከል ማዘዝ ወይም ግንባታው እንዲቆም ማገድ አለበት፡፡

3/ Even where there is an approved design, if the construction deviates from the design in a manner that causes a fundamental discrepancy, the institution shall order the demolition or modification of the newly constructed building or the renovated existing building, or it shall suspend the construction.

፬/ በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ "፫" የተገለጸው ቢኖርም ከፀደቀው ዲዛይን ውጪ በመገንባቱ እንዲፈርስ ወይም እንዲስተካከል ትዕዛዝ የተላለፈበት ህንፃ የዚህን አዋጅ እና የኢትዮጵያ የህንፃ ስታንዳርድ ግዴታዎችን የማይጥስ ሆኖ ከተገኘ ተቋሙ ተገቢውን መቀጮ እንዲከፍል በማድረግ ግንባታው እንዲቀጥል ይፈቅድለታል፡፡

4/ In spite of what is stated in sub-section 3 of this Article, to be demolished due to its construction outside of the approved design or the building ordered to be repaired does not violate the obligations of this Proclamation and Ethiopian Building Standards,if found, the facility will be allowed to continue construction by making them pay the appropriate fines.

፭/ የፀደቀ ዲዛይን ሳይኖር ወይም ከፀደቀው ዲዛይን ውጪ በመገንባቱ ዲዛይን እንዲያፀድቅ ወይም ግንባታውን እንዲስተካከል ትእዛዝ የተላለፈለት

5/ To approve the design or the construction by building without an approved design or outside of the approved design, the person to whom the order has been given to make

https://ethiodata.et/

ሰው በተሰጠው ትእዛዝ መሠረት ማከናወኑን ለተቋሙ በፅሁፍ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

፮/ ዲዛይን እንዲያፀድቅ ወይም የገነባውን እንዲያፈርስ ትዕዛዝ የተላለፈለት አሰሪ በትዕዛዙ መሠረት ያልፈጸመ እንደሆነ እንዲፈርስ ትዕዛዝ የተላለፈበትን ሕንፃ ተቋሙ በራሱ ወጪ በማፍረስ ወይም በማንሳት ላወጣው ወጪ ማካካሻ ከአሰሪው ገንዘብ ሊጠይቅ ይችላል፡፡ ዝርዝሩ ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣው ደንብና መመሪያ ይወሰናል፡፡

፯/ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ ፩ እስከ ፮ የተዘረዘሩትን ድንጋጌዎች በመተላለፍ የተሳተፈ ማንኛውም ባለሙያ፣ ስራ ተቋራጭ ወይም ባለቤት ከማካካሻ ወጭ በተጨማሪ ከአንድ ዓመት ባልበለጠ እሥራትና ከብር አስር ሺህ እስከ ሃምሳ አምስት ሺህ የገንዘብ ማቀጮ ይቀጣል፡፡

## ፵.አላግባብ ስለተሰጠ የግንባታ ፈቃድ

፩/ በዚህ አዋጅ መሠረት የህንፃ ግንባታ ፈቃድ ለመስጠት ሥልጣን የተሰጠው ባለሙያ፣ ኃላፊ ወይም የህንፃ ሹም ወይም ይህንኑ ተግባር እንዲያከናውን ኃላፊነት የተሰጠው ማንኛውም ሰው ሆን ብሎ፡-

ሀ) ህጋዊ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ለሌለው ሰው በቦታው ላይ

corrections must notify the institution in writing that he has carried out according to the order given he will have to.

6/ Any employer who was given an order to n either to obtain design approval or to demolish the constructed building fails to comply with the order, the institution may, at its own expense, demolish or remove the building and recover the costs incurred from the employer. The details shall be determined by Regulations and Directives to be issued for the implementation of this Proclamation.

7/ Any professional, consultant, involved in violating the provisions listed in sub-paragraphs 1 to 6 of this Article. A contractor or owner, in addition to compensation, shall not exceed five thousand shall be punished with a fine not exceeding.

## 40. Improper Construction Permit

1/According to this Proclamation, the professional responsible or the building authorized to issue building construction permit or any person who has been given the responsibility to perform this task:

a) Whether a construction permit has been issued to a person who does not

ለሚከናወን ግንባታ የግንባታ ፈቃድ የሰጠ እንደሆነ፣ ወይም

ለ)ለግንባታ ፈቃድ ጥያቄ በአስረጃነት የቀረበው ሰነድ ስህተት ሆኖ እያለ ለዚሁ ሰነድ ዕውቅና በመስጠት የተጠየቀውን የግንባታ ፈቃድ የሰጠ እንደሆነ፣ ወይም

ሐ)ለፕላን ስምምነት የቀረበን ማመልከቻ ተቀብሎ ከከተማው ፕላን ጋር ለማይጣጣም የግንባታ ጥያቄ የግንባታ ፈቃድ የሰጠ ወይም በዚህ መሠረት ለተከናወነ ግንባታ የህንጻ መጠቀሚያ ፈቃድ የሰጠ እንደሆነ፣

ከአምስት ዓመት እስከ አሥር ዓመት በሚደርስ ፅኑ እሥራት እና ከብር አሥራ አምስት ሺህ በማያንስና ከብር ስልሳ ሺህ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ የተመለከተው ጥፋት የተፈፀመው በቸልተኝነት የሆነ እንደሆነ በአዋጅ ቁጥር ፰፻፹፩/፪ሺ፯ በተደነገጉ ህጎች መሰረት የሚጠየቅ ይሆናል፡፡

**፵፩.የመቆጣጠር ግዴታን ባለመወጣት ህገ-ወጥ ግንባታ እንዲከናወን ስለመርዳት**

፩/ማንኛውም የግንባታ ቁጥጥር ባለሙያ፣ የህንፃ ሹም ወይም የግንባታ ሥራን

have a legal land ownership certificate, or

b) The document submitted as proof for the request for a building permit is wrong, and the request is made for the recognition of this document.whether a building permit has been issued, or

c) Received an application submitted for planning approval and issued a construction permit for a construction request that does not conform to the city plan. or if a building use permit has been issued for construction carried out accordingly,

will be punished from five years to ten years rigorous imprisonment and with a fine of not less fifiten thousand and not more than sixty thousand.

2/If the offense referred to in sub-article /1/ of this Article is committed through negligence; he will be liable according to Proclamation No. 881/2015.

41. **Helping to carry out illegal Construction by not fulfilling the duty of Supervision**

1/ Any construction inspector, the builder or anyone else who is responsible for

https://ethiodata.et/

የመቆጣጠር ኃላፊነት የተሰጠው ሌላ መንግሥት ሠራተኛ ወይም ይህንኑ ተግባር ለማከናወን በተቋሙ በውል ኃላፊነት የተሰጠው ሰው ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ጥቅም ለማግኘት ወይም ማስገኘት በማሰብ በዚህ አዋጅ መሠረት ሊከናወን የሚገባውን የቁጥጥር ሥራ ሳያከናውን በመቅረት በህግ የተደነገጉትን ግንባታ ደንቦች ሳይከተል እየተከናወነ የሚገኘውን የግንባታ ሥራ ሳያስቆም ወይም እንዲቆም ሳያስደርግ ግንባታውየተጀመረ፣ የቀጠለ ወይም የተጠናቀቀ እንደሆነ፤ ከአምስት ዓመት እስከ አሥር ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት እና ከአሥር ሺህ ብር እስከ ሃምሳ ሺህ ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

supervising construction work a government employee or a person contracted by the Institution to perform the same task for himself or another. The control work that should be carried out according to this Proclamation with the intention of obtaining or obtaining benefits without stopping the construction work that is being carried out without following the construction Regulations prescribed by Law or whether the construction is started, continued or completed without causing it to stop, from five years to ten years and will be punished with imprisonment of up to tem thousand to ten thousand to fifty thousand.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ የተመለከተው ጥፋት የተፈፀመው በቸልተኝነት የሆነ እንደሆነ በአዋጅ ቁጥር ፰፻፹፩/፪ሺ፯ በተደነገጉት ህጎች መሰረት የሚጠየቅ ይሆናል፡፡

2/ Proclamation No.881/2006 states that the offense referred to in sub-article /1/ of this Article was committed through negligence it will be required according to the prescribed laws

**፵፪. ባለጉዳይን ማጉላላት/ ያለአግባብ ጉዳይን ማጓተት**

**42. Exaggerating the case/unreasonably delaying the Case**

፩/ማንኛውም የሕንጻ ዲዛይን ማጽደቅ፣ የግንባታ ቁጥጥር ሥራ ባለሙያ፣ የህንፃ ሹም ወይም ይህንኑ ተግባር እንዲያከናውን ኃላፊነት የተሰጠው የተቋሙ ሠራተኛ ወይም በየደረጃው የተለያዩ መረጃዎችን ወይም ሰነዶችን ለመስጠት ኃላፊነት

1/ Any building design approval, construction control professional, the building or similar activities.The employee of the institution who is responsible for carrying out various information or documents at each level, the employee of the Institution who is responsible for giving, in the matter

የተሰጠው የተቋም ሠራተኛ በሀላፊነቱ ወይም በስራው ምክንያት በቀረበላት ጉዳይ ላይ ጥቅም ካለው ማንኛውም ሰው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ጥቅም ለማግኘት ወይም በጉዳዩ ጥቅም ያለውን ሰው ለመጉዳት በማሰብ ያለ በቂ ምክንያት በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም አሰራር ውጭ ያለበቂ ምክንያት ጉዳዩ ላይ ያልወሰነ ያዘገየ ወይም ባለጉዳዩን ያጉላላ እንደሆነ ከአንድ አመት እስከ አራት ዓመት ሊደርስ በሚችል ቀላል እሥራት እና ከብር አምስት ሺህ እስከ ብር አስር ሺህ በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

presented to him due to his responsibility or work Any person who has a benefit, directly or indirectly, or who has benefit in the matter With the intention of harming a person, without reason, by a rule, instruction or procedure issued in accordance with this Proclamation,6 months for delaying the decision on the case or exaggerating the case without any reason three years of easy work and five hundred to three thousand shall be fined.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስአንቀጽ /፩/ የተመለከተው ጥፋት የተፈፀመው በቸልተኝነት የሆነ እንደሆነ በአዋጅ ቁጥር ፰፻፹፩/፪ሺ፯ በተደነገጉ ህጎች መሰረት የሚጠየቅ ይሆናል፡፡

2/ If the offense referred to in sub-article /1/ of this Article was committed through negligence, it will be requested according to the laws stipulated in Proclamation No.881/2006.

## ፵፫.መረጃ ስለመደበቅ ወይም የተሳሳተ መረጃ ስለመስጠት

## 43.About Biding Information or giving wrong Information

፩/ ማንኛውም ከግንባታ ሥራ ጋር በተያያዘ የቦታ አጠቃቀምና ይዞታን፣ እንዲሁም በዚህ አዋጅ መሠረት ከግንባታ ሥራ አፈፃፀም ጋር ተያያዥነት ያላቸውን መረጃዎች የማስፈር፣ ሰነዶችን የመያዝ ወይም የመጠበቅ፣ የሰነዶችን ትክክለኛነት የማረጋገጥ ወይም የመስጠት ኃላፊነት

1/ Any land use and possession related to construction work, as well as from construction work in accordance with this Proclamation. To register the information related to the performance, to hold or protect the documents, the accuracy of the documents, the government employee who is responsible for verifying or giving

https://ethiodata.et/

የተሰጠው የመንግሥት ሠራተኛ በጉዳዩ ጥቅም ያለውን ሰው ለመጥቀም ወይም ለመጉዳት ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ፡-

ሀ) በሕንጻ የዲዛይን፣ የግንባታ እና ሌሎች ተዛማጅ ሰነድ ያልተረጋገጠ መረጃ ወይም በሕንጻ ዲዛይን፣ ግንባታ እና ሌሎች ተዛማጅ ሰነድ ከሚያስረዳው የተለየ መረጃ የሰጠ እንደሆነ፣ ወይም

ለ) በትክክል መግለጽ ያለበትን ተጨባጭ የሕንጻ የዲዛይን፣ የግንባታ እና ሌሎች ተዛማጅ ሁኔታዎች የሚያስገኘውን ውጤት ለማስቀረት ወሳኝነት ያለውን ፍሬ ነገር ያስቀረ እንደሆነ፤

ሐ)የተሳሳተው መረጃ የተሰጠው መረጃው የሚያስከትለውን ጉዳት ለመረዳት የሙያ ዕውቀቱ ወይም የሥራው ኃላፊነት በሚፈቅድለት ሠራተኛ የሆነ እንደሆነ፤

ከአምስት ዓመት እስከ አሥር ዓመት በሚደርስ እሥራት እና ከብር አሥር ሺህ እስከ ብር ሃያ ሺህ በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ የተመለከተው ጥፋት የተፈፀመው በቸልተኝነት የሆነ እንደሆነ በአዋጅ ቁጥር

benefits to the person who has the benefit of the case or with the intention of harming or obtaining or obtaining an improper advantage for himself or another person:

a) information not verified by building design, construction and other relevant documents or by building design, construction and others if the related document provides different information, or

b) The result of the actual building design, construction and other related conditions that must be accurately described.That he has omitted the essential material to be avoided;

c) The responsibility of the professional or the work to understand the harm caused by the information provided by the wrong information. According to the worker who allows him, we will pay ten thousand to ten thousand for five to ten years of work.

2/ Proclamation No.881/2006 states that the offense referred to in sub-article /1/ of this Article was committed through

፰፻፹፩/፪ሺ፯ በተደነገጉ ህጎች መሰረት የሚጠየቅ ይሆናል፡፡

## ፵፬. በሰነድ የአላግባብ ስለመገልገል

፩/ማንኛውም በዚህ አዋጅ የተደነገጉትን ለማስፈፀም የተመደበ የመንግሥት ሠራተኛ በሥራው አጋጣሚ ከእጁ ሊገቡ የቻሉትን የሕንጻ ዲዛይን፣ የግንባታ እና ሌሎች ተዛማጅ ሰነዶች በማጥፋት፣ በማበላሸት፣ በመደበቅ ወይም ወደ ሀሰት በመለወጥ፣ በመደለዝ ወይም በማሻሻል ወይም በከፊል ቃሉን በመቀነስ ወይም ሌላ በመጨመር እና ለግል ጥቅም አገልግሎት በሚሰጡ አኳኋን ለራሱ ከተጠቀመባቸው ወይም የተጠቀመባቸው ከሆነ ወይም ሌላ ሰው እንዲገለገልባቸው ያደረገ እንደሆነ ከአምስት ዓመት እስከ አሥር ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት እና ከብር ሃያ ሺ እስከ ብር ሃምሳ ሺህ በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (፩) ስር የተደነገገው ድርጊት የተፈጸመው የተገለፁትን ሰነዶችን የመያዝ ወይም የመጠበቅ፣ወይም አያያዛቸውን እና አጠባበቃቸውን ለመቆጣጠር ኃላፊነት በተሰጠው ሰው እንደሆነ ቅጣቱ ከአምስት ዓመት እስከ ሀያ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት እና ከብር ሃያ ሺህ እስከ ብር መቶ ሺህ በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ

negligence.

## 44. Documenting Abuse

1/Any government employee who is assigned to carry out the provisions of this decree shall, on the occasion of his work, be destroying, mutilating, concealing or falsifying all architectural design, construction and other related documents.By altering, diluting or modifying or by subtracting or otherwise adding to the word for himself in a manner that provides service if you use them or use them or someone else As long as he has served them, he will be sentenced to five to ten years of hard labor and up to twenty thousand.

2/ The actions prescribed under sub-article (1) of this Article are carried out to keep or protect the specified documents. or if it is by the person responsible for handling and maintaining them, the punishment is from five years to twenty five years in prison and a fine of up to 20,000 to 100,000 Birr he will be punished.

https://ethiodata.et/

ይቀጣል፡፡

፫/በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ጥፋት የተፈፀመው በቸልተኝነት የሆነ እንደሆነ ከሶስት አመት እስከ አምስት አመት ሊደርስ በሚችል እስራትና ከብር ሦስት ሺህ እስከ ብር ስድስት ሺህ በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

3/If the offense referred to in sub-article /1/ of this Article is committed through negligence, he will be punished from three years to five years in prison and a fine of up to 3,000 to 6,000 Birr.

**፵፭.ደረጃው የማይፈቅድለት ወይም ተገቢው ፈቃድ ሳይኖረው ግንባታ ስለማከናወን**

ማንኛውም የተመዘገበ ሥራ ተቋራጭ በዋናነት ወይም በንዑስ ሥራ ተቋራጭነት አግባብነት ባለው አካል የተሰጠው የሙያ ደረጃ የማይፈቅድለትን የግንባታ ሥራ አከናውኖ የተገኘ እንደሆነ ወይም አግባብ ካለው አካል የተሰጠ የሙያ ፈቃድ ሳይኖረው በባለሙያ ሊሰራ የሚገባውን ግንባታ ሠርቶ የተገኘ እንደሆነ ከአምስት ዓመት እስከ አሥር ዓመት በሚደርስ ፅኑ እሥራት እና ከብር አምስት ሺህ እስከ ብር አሥር ሺህ በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡

**45. For Carrying out Construction that the Standard does not allow or without the Appropriate Permission**

Any registered contractor is principally or subcontractor of the profession assigned by the relevant body found to have performed construction work that is not allowed by the standardor without a professional license issued by the relevant body as it is obtained by doing the construction that should be done by a professional, from five years to ten years of hard work and he will be punished with a fine ranging from five thousand to ten thousand.

**፵፮.ደረጃውን ያልጠበቀ ግንባታ ስለማከናወን**

፩/ማንኛውም የተመዘገበ ሥራ ተቋራጭ በዋናነት ወይም በንዑስ ስራ ተቋራጭነት ሲሰራ፡-

**46.For carrying out non-standard Construction**

1/ Any registered contractor working as principal or sub-contractor:

https://ethiodata.et/

ሀ)ዲዛይኑ የሚጠይቀውን የግንባታ ቁሳቁስ ደረጃ ባለመጠበቅ የጥራት ወይም የጥንካሬ ደረጃውን ባላሟላ የግንባታ ዕቃ ወይም በሙያው ዘርፍ ተቀባይነት ያለውን አሰራር ሳይከተል የሰራ እንደሆነ፣ ወይም

ለ)በዲዛይን ወይም በሌሎች የውለታ ሰነዶች በግልጽ የተመለከቱ የሥራ ሁኔታዎችን በባለሙያ ሊለዩ የሚችሉና ተገቢውን ሙያዊ ጥንቃቄ አድርጎ ቢሆን ኖሮ ሊታረሙ ይችሉ የነበሩ ስህተቶችን ሳያርም ወይም እንዲታረሙ ሳያደርግ ያከናወነው ግንባታ አደጋ ያስከተለ እንደሆነ፣ ከአምስት ዓመት እስከ አሥር ዓመት በሚደርስ ፅኑ እሥራት እና ከብር ሃምሳ ሺህ እስከ ብር መቶ ሺህ ድረስ ይቀጣል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከቱት ጥፋቶች የተፈፀሙት በቸልተኝነት የሆነ እንደሆነ ቅጣቱ ከአንድ ዓመት እስከ አምስት ዓመት ሊደርስ በሚችል እሥራትና ከብር አንድ ሺ. እስከ ብር አምስት ሺ. በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይሆናል፡፡

a) Building material that does not meet the quality or strength level by not maintaining the standard of construction material required by the design. or that he did not follow the accepted procedure in his profession, or;

b) Those that can be identified by experts in the working conditions clearly stated in the design or other documents without correcting or causing to be corrected errors that could have been corrected with due professional care. If the construction caused an accident, he will be imprisoned for five to ten years. He will be fined up to 1,000,000.

2/ If the offenses referred to in sub-Article (1) of this Article are committed through negligence, the punishment shall be from one year to five years and a fine of one thousand to five thousand Birr.

https://ethiodata.et/

## ፵፯. <u>በአሰሪ ስለሚፈጸሙ ወንጀሎች</u>

፩/ ማንኛውም አሰሪ፦

ሀ) ለሚያከናውነው ግንባታ የሚያስፈልገውን የዲዛይን ሥራ ወይም በተሰራው ዲዛይን መሠረት የሚከናወነውን ግንባታ የሙያ ደረጃው በማይፈቅድለት ባለሙያ ያሰራ እንደ ሆነ ወይም፣

ለ) የሚያከናውነው ግንባታ ደረጃ ከሚጠይቀው የግንባታ ቁሳቁስ ያነሰ የጥራት ደረጃ ባላቸው ቁሳቁሶች በጥቅም ላይ እንዲውሉ ያደረገ እንደሆነ ወይም፣

ሐ) ከሚመለከተው አካል ተገቢውን የመጠቀሚያ ፈቃድ ሳያገኝ ግንባታውን ጥቅም ላይ ካዋለ ወይም ከተሰጠው ፈቃድ ውጪ ለሌላ አገልግሎት አውሎት የተገኘ እንደሆነ፣ ወይም

መ) በማንኛውም ሌሎች ሁኔታዎች ግንባታው የሕዝብን ደህንነት አደጋ ላይ በሚጥል ሁኔታ ያከናወነ እንደሆነ፣

ከአምስት ዓመት ባልበለጠ እሥራትና ከብር አሥር ሺህ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።

## 47. <u>**About the Crimes Committed by the Employer**</u>

1/ Any employer shall:

a) The design work required for th construction to be carried out or the construction to be carried out according to the design that he has worked as a professional whose professional standards do not allow him to do so, or

b) use of lower quality construction materials than the required construction level whether or not.

c) not using the building without obtaining the appropriate use permit from the relevant party or without the permit granted as acquired for other services, or

d) In any other circumstances, if the construction is carried out in a situation that endangers public safety, from he will be punished not more than five years and he will be fined not more than ten thousand Birr.

https://ethiodata.et/

## ፵፰.የአማካሪነት የሙያ ኃላፊነትን ስለመጣስ

፩/ማንኛውም የተመዘገበ አማካሪ ሆን ብሎ በሙያው በግልጽ የሚታወቁ ጥንቃቄዎችን ባለማድረግ፡-

ሀ) በአዋጁ፣ሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕጎችና በኢትዮጵያ የህንፃ ስታንዳርዶች የተቀመጡትን አስገዳጅ መስፈርቶች ያልተከተለ ዲዛይን ካዘጋጀ ወይም ሌሎች ተዛማጅ ሰነዶችን ካዘጋጀ፣ ከአንድ ዓመት ባልበለጠ እሥራትና ከብር አምስት ሺህ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይሆናል፡፡

ለ)እንደግንባታ ሥራው ዓይነት ሊጠበቅ የሚገባውን የጥራት ደረጃ ደንቦች በመጣስ ለግንባታው ዕቃ ለሚያቀርብ ሰው ወይም ግንባታውን ለሚያከናውነው ሥራ ተቋራጭ ለዚሁ ግንባታው ሊውል ከሚገባው ያነሰ የጥንካሬ ወይም የጥራት ደረጃ ያለው የግንባታ ዕቃ እንዲያቀርብ ወይም አገልግሎት ላይ እንዲውል ፈቃድ ወይም ስምምነት ከሰጠ፣ ወይም

ሐ) ሙያው የሚጠይቀውን ሥነ ምግባር በመጣስ በግንባታ ሙያ ዘርፍ ተቀባይነት የማይኖረው ወይም

## 48. Violation of the Professional Responsibility of a Consultant

1/ Any registered consultant who fails to take precautions clearly known in his profession:

a) Mandatory requirements set by the Proclamation, other relevant laws and Building Standards in Ethiopia, if he prepares a non-compliant design or prepares other related documents, he will be punished not more than one year imprisonment and a fine not more than five thousand Birr.

b) To the person who supplies the construction material in compliance with the quality standards that should be maintained according to the type of construction work, or for the construction contractor, the lower strength or quality standard should be used for the same construction, if he gives a license or agreement to provide or use the existing building material, or

c) Violation of the ethics required by the profession, which is unacceptable or substandard in the

https://ethiodata.et/

ከደረጃ በታች የሆነ ግንባታ እንዲከናወን ወይም የተሰራ ግንባታ ተቀባይነት እንዲያገኝ ስምምነቱን በመስጠት የሕዝብን ደህንነት ለአደጋ የሚያጋልጥ ግንባታ አገልግሎት ላይ እንዲውል ያደረገ እንደሆነ

ከአምስት ዓመት እስከ አሥራ አምስት ዓመት በሚደርስ እሥራት ወይም ከብር ሠላሳ ሺህ እስከ ብር ሰባ ሺህ በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከቱት ጥፋቶች የተፈፀሙት በቸልተኝነት የሆነ እንደሆነ ከሶስት ዓመት እስከ አምስት ዓመት ሊደርስ በሚችል እሥራትና ከብር አምስት ሺ. እስከ ብር አሥር ሺ. በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይሆናል፡፡

፫/ በአንድ ላይ በጣምራ የሚሰራ ሥራ ተቋራጭ ወይም የግንባታ አማካሪዉ ሙያው የሚጠይቀውን ሥነ ምግባር በመጣስ በግንባታ ሙያ ዘርፍ ተቀባይነት የማይኖረው ወይም ከደረጃ በታች የሆነ ግንባታ እንዲከናወን ወይም የተሰራ ግንባታ ተቀባይነት እንዲያገኝ ስምምነቱን በመስጠት የሕዝብን ደህንነት ለአደጋ የሚያጋልጥ ግንባታ አገልግሎት ላይ እንዲውል ያደረገ እንደሆነ ከአምስት ዓመት እስከ አሥራ አምስት ዓመት በሚደርስ እሥራት ወይም ከብር መቶ ሺህ እስከ ብር መቶ ሀምሳ ሺህ

construction industry. Risk to public safety by giving consent for construction to be carried out or construction to be approved as long as the exposed construction is put into service, it will last from five years to fifteen years imprisonment.

2/ If the violations referred to in sub- article /1/ of this Article are committed through negligence, the punishment will be from three years to five years and and a fine of five thousand to ten thousand Birr.

3/ An individual working in the construction industry or as a construction professional is required to adhere to professional ethics, if they fail to do so or if the construction carried out does not meet the required standards, or if the constructed work does not meet the required criteria, the service may be subject to legal penalties. If the construction poses a danger to public safety, those responsible may face fines ranging from five years to up to fifteen years, or fines ranging from 100,000 to

https://ethiodata.et/

በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

150,000 Ethiopian Birr.

## ፵፱. ስለሙያና ሥራ ፈቃድ ዕገዳ

በዚህ ክፍል በተመለከቱት ወንጀል ድርጊቶች ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ የተመዘገበ ባለሙያ ወይም አማካሪ ወይም ሥራ ተቋራጭ በፍርድ ከተወሰነበት ቅጣት በተጨማሪ ፍርድ ቤቱ ጥፋተኛው ከአምስት ዓመት ጀምሮ ጥፋተኛ በተባለበት አንቀጽ እስከተመለከተው ከፍተኛው የእሥራት ዘመን ድረስ የሙያ ወይም የሥራ ፈቃዱ ሊታገድ ይችላል፡፡

## 49.Restrictions on profession and Employment

A registered practitioner or consultant or profession found guilty of the offenses referred to in this section if the contractor is sentenced by the court, in addition to the penalty, the court will punish the offender for five years. The professional or work license may be suspended for the maximum period of service specified in Article.

## ክፍል አስር
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## PART TEN
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

## ፶.ስለይግባኝ ሰሚ ቦርድ

፩/የህንጻ አዋጁ ተግባራዊ በሚሆንባቸው ከተሞች ከግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ስራዎች ጋር ተያይዞ የሚነሱ ቅሬታዎችን በመመርመር ውሳኔ የሚሰጥ ተገቢው የሙያ ስብጥር ያላቸው አባላት የሚገኙበት የይግባኝ ሰሚ ቦርድ ይህን አዋጅ ተከትሎ በሚወታው ደንብ መሰረት ይቋቋማል፤

፪/ ይግባኝ ሰሚ ቦርዱ አባላት አደረጃጀትና የሥራ ድርሻ ሁኔታ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣው ደንብ ይወሰናል፤

## 50. APPEAL HEARING BOARD

1/An Appeals Board shall be established in accordance with this Proclamation, which shall include members of the appropriate professional composition who shall investigate and resolve complaints related to construction permit and supervision activities.

2/The Board of Appeals members’ role shall be determined by the Regulations issued for the implementation of this Proclamation.

https://ethiodata.et/

፫/ ቦርዱ በሕንፃ ግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ተቋም በተሰጡ ውሳኔዎች ላይ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን በይግባኝ አይቶ የመወሰን ሥልጣን ይኖረዋል፡፡በውሳኔው ያልረካ አካል ጉዳዩን ወደመደበኛ ፍርድ ቤት መውሰድ ይችላል፡፡

## ፶፩.የሚኒስቴሩ ሥልጣንና ተግባር

ሚኒስቴሩ ይህን አዋጅ እና አዋጁን ለማስፈጸም የሚወጡ ደንብና መመሪያ በማስፈፀም ረገድ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

፩/ ይህን አዋጅና የሕንፃ ደንብ ለማስፈፀም የሕንፃ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፪/ በአገር አቀፍ ደረጃ የሚሠራባቸው ልዩ ልዩ ኮዶችና ስታንዳርዶ ያዘጋጃል፣ወይም እንዲዘጋጅ ያደርጋል፤

፫/ ለየሕንፃ ምድቦቹ የሚያገለግሉ የዲዛይንና ኮንስትራክሽን ዘዴ መመሪያዎች ሞዴል ለክልሎች ያዘጋጃል፤

፬/ አዋጁ በክልሎችና በሁለቱም ከተማ አስተዳደሮች እንዲሁም እንደአስፈላጊነቱ አዋጁ ተፈፃሚ በሚሆንባቸው ከተሞች ያለውን አተገባበር በተመለከተ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፤

3/ The Board shall have the power to hear and decide appeals against decisions made by the Building Construction Licensing and Supervision Institution. The party who is not satisfied with by the decision may submit the matter to the competent ordinary court.

## 51. Powers and Duties of the Ministry

The Ministry shall have the following powers and duties in the implementation

of this Proclamation,Regulations and Directives;

1/ It may issue building directives for the implementation of this Proclamation and Building Regulations.

2/ Prepares, or makes, various codes and standards for use at the national level;

3/ Develop a model for the design and construction guidelines for the building categories;

4/ Monitor and support the implementation of the Proclamation in the Regions and in both City Administrations as well as in the cities where the Proclamation is to be implemented;

https://ethiodata.et/

፭/ ከሌሎች አግባብ ካላቸው የፌደራል መንግስቱ አካላት ጋር በመቀናጀት ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች አዋጁን ለማስፈጸም እንዲችሉ የአቅም ግንባታና የቴክኒክ ድጋፍ ያደርጋል፡፡

## ፶፪.የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ይህ አዋጅ ስራ ላይ ከዋለበት ቀን በፊት አዋጁን ተከትሎ የወጡ የህንፃ ደንብ ቁጥር ፪፻፵፫/፪ሺ፫ እና የህንፃ መመሪያ ቁጥር ፭/፪ሺ፫ ለሁለት አመት እስኪሻሻሉ ድረስ በስራ ላይ ይሆናሉ፡፡

## ፶፫.የተሻሩና ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች

፩/የህንፃ አዋጅ ቁጥር ፮፻፳፬/፪ሺ፩ እና ይህን አዋጅ ተከትለው የወጡ ደንብና መመሪያ በዚህ አዋጅ መሰረት ተሽሯል፡፡

፪/ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሕግ ወይም ልማዳዊ አሠራር በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

## ፶፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

5/ Coordinate capacity building and technical support for Rregional and City Administrations to implement the Proclamation in collaboration with other stakeholders.

## 52. Transitory Ordinance

Building Regulation No.243/2003 and Building Directive No.5/2003 issued beforethe date of entry into force of this Proclamation shall remain in force for two years until amended.

## 53.Repealed And Ineffective Laws

1/ Building Proclamation No.624/2001 was repealed in accordance with this Proclamation.

2/ Any law or customary practice which is inconsistent with this Proclamation shall not apply to matters covered by this Proclamation.

## 54. EFFECTIVE DATE

This Proclamation shall enter into force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazeta.

https://ethiodata.et/

አዲስ አበባ ሚያዚያ ፴ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም

Addis Ababa.7th May 2024

**ታዬ አጽቀሥላሴ**
**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**TAYE ASTEK-SELLASIE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

https://ethiodata.et/